


## አብን የባልደራስ-መኢአድን ጥምረት ሊቀላቀል ነው

ገጽ 4



# ባልደራስ

1ኛ ዓመት ቁጥር 05 ጥር 29 ቀን 2013 ዓ.ም.


## አዲስ አበባን የማውደም እንቅስቃሴ ይቁም!

# መንግሥት ባልደራስ የጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ ከለከለ





## ፍርድ ቤቱ ሆይ!

### አስካለ ደምሌ፤ ከቃሊቲ ወህኒ ቤት (የፖለቲካ እስረኛ)

“መንግሥት ላይ ጫና መፍጠር እና የእርስ በእርስ ግጭት ማስነሳት” በሚል ክስ ተመስርቶብኝ እስር ቤት ሆኜ ጉዳዬን እየተከታተልኩኝ መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ለመታሰሬ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከመከሰቱ በፊት፡-

1. በመንግሥት ተቋም ውስጥ በምሠራበት ወቅት በእያንዳንዱ እንቅስቃሴዬ ልክ መንግሥታዊ የስለላ አባላትን በመመደብ፣ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የብልጽግና ፓርቲ አመራሮች “መንግሥት ደሞዝ እየከፈለሽ በባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ መሳተፍ የለብሽም” ብለው በአካል እና በስልክ ተፅዕኖ ሲፈጥሩብኝ ነበር።

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የኢትዮ ቴሌኮም ሽያጭ ጥቅምና ጉዳት

## ውስጠ ወይራው ያለመለወጥ ‹ለውጥ›

# አዲስ አበባን የማውደም እንቅስቃሴ ይቁም !

በአዲስ አበባ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት አጠገብ የሚገኘው የደጃዝማች አስፋው ከበደ ቤት የነበረ ቅርስ በኦሕዴድ/ብልፅግና ፈርሷል። በምትኩም የኦሕዴድ ወታደራዊ ካምፕ እንደሚሠራበት ተነግሯል። ይህም በአቶ ሽመልስ አብዲሳ የተነገረው ከተማዋን በስውር የማውደም ስትራቴጂ አካል ነው። ታሪክ እያጠፉ የወታደር ጎጆ መቀለስ ሀገር አውዳሚነት ነው። ፀረ ኢትዮጵዊነት ነው። አሁንም ቅርሱ ታድሶ ወደነበረበት ገፅታ ሊመለስ ይገባል። አፍራሾች የአዲስ አበባን ሕዝብ በይፋ ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል። ሕዝቡም ይህ እንዲሆን መጠየቅ አለበት። ይህንን የማድረግ ሚናው የደጃዝማች አስፋው ቤተሰቦች ብቻ መሆን የለበትም። ተረኛው ኦሕዴድ/ብልፅግና ሀገር አውዳሚነቱን በአስቸኳይ ሊያቆም ይገባል። አዲስ አበባ የኦሕዴድ እስር ቤት አትሆንም።

የሕወሓት ልዩ ጥቅም ማዕከል የነበሩት ከአማራ የነጠቃቸው ራያና ወልቃይት ነበሩ። የኦሕዴድ ደግሞ አዲስ አበባ ሆናለች። አሁን ከልዩ ጥቅምም ታልፎ ከተማዋን የማጥፋት ተግባር ነው የተያዘው። በመሆኑም የአዲስ አበባ ሕዝብ ብሎም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አባቶቹ በገነቧት ከተማ ፍርስራሽ ላይ ለመቆም መፍቀድ የለበትም።


**ባልደራስ ጋዜጣ**
መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም.
ተመሰረተ

በየ15 ቀኑ የሚታተም

**አሳታሚ**
ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ)

**ዋና አዘጋጅ**
ጌጥዬ ያለው
ክፍለ ከተማ፡- ቂርቆስ
ወረዳ፡- 02 የቤት ቁጥር፡- አዲስ
ስልክ፡- +2519 24 51 70 77
ኢ-ሜይል፡- newsgett@gmail.com

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ወግደረስ ጤናው

**አምደኞች**
ገለታው ዘለቀ
ኢንጂነር ጌታነህ ባልቻ

**አርታዒ**
መሰበወርቅ ቅጣው
ነብዩ ውብሸት

**ፀሐፊ፡-** ሕይወት ዳዊት

**የገፆች ቅንብር** ሐብ-ዲዛይን

**ገፀ ድር አስተዳደር** ኢስያስ ፅጉ

# መንግሥት ባልደራስ የጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ ከለከለ

ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) የሚያስተባብረው የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ በአዲስ አበባ እና በልዩ ልዩ የውጭ ሀገራት ከተሞች ሊካሄድ ታቅዷል። ይሁን እንጂ እሁድ ጥር 23 ቀን 2013 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ሊከናወን የነበረውን ትዕይንተ ሕዝብ በኦሕዴዱ አዳነች አቤቤ የሚመራው የአዲስ አበባ ከንቲባ ፅህፈት ቤት ከልክሏል።

በተቃውሞ ሰልፉ አራት ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ማለትም በአማራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን መንግሥታዊ ጅምላ ጭፍጨፋ፣ የባልደራስ አመራሮችን ፖለቲካዊ እስር፣ በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉ የኦሮሞ ጅምላ ሕንፃዎችን እንዲሁም ሱዳን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ጥሳ መግባቷን የሚያንፀባርቁ የተቃውሞ ድርምፆች እንዲሰሙ ታቅዷል። እነኚህን አጀንዳዎች ማዕከል ያደረገ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ በአውሮፓ፣ በሰሜን አሜሪካ እና በሌሎችም የውጭ ሀገራት ከተሞች ይካሄዳል። በአዲስ አበባ የሚከናወነውን ሰልፍ መንግሥት ሦስቱን ነጥቦች ጠቅሶ ሲከለክል በአማራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ጅምላ ጭፍጨፋ ግን ሳይጠቅስ አልፎታል። ይህም መንግሥት ጅምላ ጭፍጨፋውን ክዶ አለመቅረቡን ያሳያል።

ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የዜጎች መብት እንደሆነ ይታወቃል። መንግሥትም የተቃውሞ ሰልፉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ፀጥታ የማስከበር ግዴታ እንጂ የመከልከል መብት አልነበረውም።

# አብን የባልደራስ-መኢአድን ጥምረት ሊቀላቀል ነው

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) የባልደራስ- መኢአድን ጥምረት በመቀላቀል መጭው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ከባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) እና ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ጋር በቅንጅት እንደሚሰራ ይፋ አድርጓል፡፡ ይህም የመራጮች ድምፅ እንዳይከፋፈል ያግዛል፡፡ ሦስቱ ፓርቲዎች ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት እየሰሩ ሲሆን በተለይ በአዲስ አበባ ፖለቲካ ላይ ተመሳሳይ አቋም አላቸው፡፡ ከተማዋ የሁሉም ነዋሪዎቿ እንደሆነች ያምናሉ፡፡ በአዲስ አበባ ላይ የኦሮሞ ልዩ ጥቅም እንዲሰጠው የሚደነግገውን አፓርታይዳዊ አዋጅ ይቃወማሉ፡፡

የሦስቱ ፓርቲዎች ጥምረት አስቀድሞ በሕዝብ፣ በፓርቲዎቹ መካከለኛ አመራሮች አባላት ዘንድ ሲቀርብ የቆየ ጥያቄ ነው፡፡

# የእነ ፋኖ ቻላቸው እንየው የክስ መዝገብ ተዘጋ

በጎንደር አንገረብ ወህኒ ቤት በእስር ላይ ያሚገኙት በእነ ፋኖ ቻላቸው እንየው መዝገብ የተከሰሱ ስምንት ፋኖዎች የክስ መዝገብ ተዘግቷል። ፍርድ ቤቱ ጥር 21 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መዝገቡን የዘጋው ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ በቂ ምስክር ማቅረብ ባለመቻሉ ነው።

ከተከሳሾች መካከል የፋኖ ሊቀ መንበር ሰሎሞን አጠናው፣ ቻላቸው እንየው፣ ሚናስ አለማየሁ እና ዮሃንስ ዘላለም ይገኙበታል። የአማራ ፋኖ አደረጃጀት በአሁኑ ጊዜ ያለ መንግሥት እገዛ የሱዳንን ወራሪ ጦር ወደ መሀል ጎንደር እንዳይገባ እየመከተ እና የኢትዮጵያን ግዛት ሙሉ በሙሉ ለቆ እንዲወጣ እያጠቃ ይገኛል። ከወያኔ ጋር በተደረገው ጦርነትም ከፍተኛ ድል አስመዝግቧል። ይሁን እንጂ መንግሥት ተገቢውን እውቅና ነፍጎታል።

# የእነዋለልኝ መኮንን ትግል የተላላኪነት ሚና እንደነበር ምሁራን ተናገሩ

በኢትዮጵያ የብሔር ፖለቲካ ጠንሳሽ እንደነበር የሚነገርለት ዋለልኝ መኮንን እና በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ የነበሩ የትግል አጋሮቹ የጀብሀ መልዕክተኞች እንደነበሩ ምሁራን ተናግረዋል። በወቅቱ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩትና በተለያዩ የፖለቲካ ትንታኔያቸው የሚታወቁት ብሎም የ‹ሀገራዊ ብሔርተኝነትና ዘውጋዊ ብሔርተኝነት በኢትዮጵያ› መጽሐፍ ደራሲ አቶ አምሀ ዳኘው ዋለልኝ መኮንን የአማራ ተወላጅ ቢሆንም የተገንጣይ ፖለቲካ አቀንቃኙ የጀብሀ ተላላኪ እንደነበር እማኝ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። አቶ አምሀ ይህንን ያሉት ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ባደረጉት ንግግር ነው። እንደ እሳቸው ማብራሪያ ‹የብሔሮች ጥያቄ በኢትዮጵያ› በሚል ርዕስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ በተማሪዎች መድረክ ላይ በዋለልኝ መኮንን የተነበበውና ‹ታገል› በተሰኘው የተማሪዎች ጋዜጣ የታተመው ባለ አምስት ገፅ ሁፍ በጀብሀ የተፃፈ እንደነበር ገልፀዋል።

ዶ/ር በቃሉ አጥናፉ በኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ አስተማሪና ተመራማሪ የሆኑት ምሁር በበኩላቸው ዋለልኝ ፖለቲካዊ ሀሳቦችን የሚያብሰለስል በሳል አዕምሮ እንዳልነበረው በመግለጽ ‹‹ዋለልኝ የሰነቀረው ነገር ነው፣ ለዚህ ፖለቲካዊ ዝቅጠት›› የዳረገን ሲሉም ተደምጠዋል።

በአንጻሩ ባለፈው ዓመት መንግሥት ባዘጋጀውና የኦሮሞ እና የትግራይ ፅንፈኛ ፖለቲከኞች ተመርጠው በታደሙበት የዋለልኝ መኮንን 50ኛ ዓመት ዝክረ በዓል ላይ የተገኙ የኦነግ እና የመኢሶን አባላት የነበሩ የተማሪዎች ንቅናቄ ተሳታፊዎች ጽሁፉን ራሳቸው ተማሪዎች በጋራ አዘጋጅተውት በዋለልኝ መነበቡን ገልጸው ነበር። ከእነዚህም መካከል ዲማ ነግዎ ይጠቀሳሉ።

# ውስጠ ወይራው ያለመለወጥ ‹ለውጥ› (፪)

በቃሉ ሰው መሆን፤ የሕግ ባለሙያ
Email = beqalubelete@gmail.com

በክፍል አንድ መጣጥፌ ‹ለውጥ› እየተባለ የሚወራው ሀሰት መሆኑን አብራርቻለሁ። ‹ለውጥ› ተብየው ውስጠ ወይራ እንደሆነ እና ‹የለውጡ› መሪ ነኝ ባዩ አብይ አሕመድ ነብረው የወጡት ወያኔ የጣለውን እንቁላል እንደሆነ አብራርቻለሁ። በ‹ለውጥ› ሽፋን ‹ለውጥን› የመከላከል ቁልቁለቱ አያሌ ርዕዮተ ዓለማዊ፣ ሕገ መንግሥታዊ፣ ተቋማዊ እና ሥርዓታዊ መገለጫዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል ሦስት መገለጫዎችን ቀንጭቤ አገልፃለሁ። አንደኛው የአዳፍኔነትና የአስቀጣይነት መንታ ስለት ሲሆን ይህንን ባለፈው ክፍል በዝርዝር አይተናል። በዛሬው ክፍል ደግሞ ሁለቱን ቀጥሎ እናያለን፡-

ለ/ የውርስ እዳ ደብዳቤውን ማን ይቅደደው?

የህወሀት ህገመንግሥት በጥቅሉ በተቃርኖ የተሞላ፣ ሃገሪቱን በመንታ ስለት የሚገዘግዝ፣ የሀገር ብተናን የጸነሰ ስታሊናዊ የትግል መሳሪያ ስለመሆኑ ነጋሪ አያሻውም። የተቃርኖው ዋና መሠረት የሚቀዳው ሕገመንግሥቱ ስታሊናዊ መአከላዊነትን ከፌደራሊዝም ጽንሰ ሀሳብ ጋር ለማዳቀል ከመሞከሩ ላይ ነው። ተረገጥ ወይ ተገንጠል በሚል መልኩ በአንድ በኩል የብሄረሰብ መብት ጠበቃነት ስም እስከመገንጠል የሚደርስ የተለጠጠ መብት ይሰጥና በሌላ በኩል ከመገንጠል በመለስ ያሉ ፍትሃዊ የብሄር መብቶችን ይደፈጥጣል፤ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን ያሰፍርና በግልባጭ እኔ ልወቅላቹ የሚል ጠቅላይ ስርአት ይዘረጋል፤ በፌደራላዊ መዋቅር ስልጣንን የጎንዩሽ ያከፋፈለ መስሎ፤ እንዲሁም የመንግሥትን ሥልጣን በሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ መካከል የሥልጣን ክፍፍል መርህን የተከተለ መስሎ በግልባጭ



ስልጣንን በአንድ ጠቅላይ ኃይል ስር የሚያከማች ስታሊናዊ የተዋረድ የእዝ ሰንሰለት/vertical delegation በማስፈን የተማከለ አስተዳደር ይጋብዛል። የሰብአዊ መብቶችን ዘርዝሮ ያሰፍርና በግልባጭ በዝርዝር ህጎች የሚታገዱበትን ስልት ይቀይሳል፣ ለመከበራቸውም ተቋማዊ ዋስትና አይሰጥም፤ መድበለ ፓርቲ ስርአት አሰፈንኩ ይልና በግልባጭ የአውራ ፓርቲ አገዛዝን ያሳልጣል፤ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ እንዳለው ይደነግግና በግልባጭ እስከመገንጠል መብት ይሰጣል፣ የሀገር ሉአላዊነትን እውቅና ይነሳል። ከላይ ለማሳያነት የተገለጹትን ህጸጾችንና መሰል ሰንኮፎችን መጸነሱን ስንመለከት ሀገሪቱ አሁን ለደረሰችበት በተቃርኖ የመሰቀዝ እና የፖለቲካ ቀውስ ዋና መሰረቱ የህወሃት ህገመንግሥት እና ሕገመንግሥቱ የተመሠረተበት የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት እንዲሁም ዘር ላይ የተመሠረተው የፌደራል አወቃቀር እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም።

በመሆኑም የሀገሪቱን የፖለቲካ ቀውስ መሠረታዊ ፈውስ ለመስጠት ሕገመንግሥቱ ከሚደነግገው ማሻሻያ ስርአት ውጪ በሆነ ዘዴ ሕዝባዊ ሕገመንግሥት ከመዘርጋት መጀመር አለበት። ሕገመንግሥታዊ “ማሻሻያ” ሲወሳ ከቃላት አጠቃቀም ጀምሮ መጤን ያለባቸው መሠረታዊ ተጠየቆች አሉ፤ እነሱም ሕገመንግሥቱ በምን ዘዴ፣ መቼ እና በምን ያህል መጠን ይሻሻል የሚሉት ጭብጦች ናቸው። በሕገመንግሥቱ ላይ ስርነቀል ንቅለተከላ መደረግ አለመደረጉ ላይ መሠረታዊ አንድምታ የሚያሳድሩ ጭብጦች ናቸው። በምን ዘዴ እና መቼ ይሻሻል ለሚሉት ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ በምን ያህል መጠን ይዘቱ ይቀየር የሚለውን የሚመልሱ ናቸው። 1ኛ በምን ዘዴ የሚለው በዋናነት ሕገመንግሥቱ እራሱ በዘረጋው የማሻሻያ ስርአት ወይስ ከሕገመንግሥቱ መአቀፍ ውጪ በሆነ መንገድ የሚለው ላይ ያጠነጥናል፤ ሕገመንግሥቱ እራሱ በዘረጋው ስርአት ለማሻሻል መሞከር ሕገመንግሥቱ መሠረታዊ መርሁን እንደያዘ ቁንጽል ማሻሻያ በማድረግ የማስቀጠል ውጤጥ ያስከትላል። ምክንያቱም በመሠረታዊነት የማሻሻል ፍላጎት ቢኖር እንኳ የማሻሻያ ስርአቱ የሚፈቅድ አይሆንም። ይህ ደግሞ ሕገመንግሥቱ ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ፋይዳ የሚኖረው ለራሱ ለሕገመንግሥቱና ደራሲዎቹን ነው።

በአንጻሩ የሀገሪቱ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ የሚጠይቀው ደግሞ በሕዝብ ለሕዝብ ውይይት እና ድርድር የግለሰብ እና የቡድን መብትን አጣጥሞ የሚያስኬድ እና ወቅቱን የዋጀ አዲስ ማህበራዊ ውል ማሰርን ነው። በመሆኑም ሕገመንግሥቱ ከዘረጋው የማሻሻያ ስርአት ውጪ ሕገመንግሥታዊ ንቅለ ተከላ ማድረግ አልያም ጥንተ መሠረታችንን ያስጠበቀ አዲስ ማህበራዊ ውል መዋዋል ያስፈልጋል። 2ተኛ “ማሻሻያ” መቼ መከናወን አለበት፤ በዋናነት በሽግግር ወቅት ሁኖ፣ ከምርጫ በፊት ወይስ በኋላ በሚለው ጭብጥ ላይ የሚያጠነጥነው ነው። የዓለም አቀፍ ንጽጽራዊ ሕገመንግሥታዊ ሕግ/ comparative constitutional law ተሞክሮ የሚያሳየው ስርነቀል ሕገመንግሥታዊ ንቅለተከላ ለማከናወን ትክክለኛው ወቅት በሽሽግር ወቅት ሁኖ ከምርጫ በፊት መከናወን እንደሚገባው ነው። ከምርጫ በኋላ ስርነቀል ሕገመንግሥታዊ ንቅለተከላ ለማድረግ የሚቻልበት እድል እጅግ ጠባብ ነው። ምክንያቱም በዋናነት ከምርጫ በኋላ የሚደረግ ማሻሻያ ሕገመንግሥቱ የዘረጋውን ስርአት ተከትሎ ለማሻሻል ስለሚገደድ ነው። ሕገመንግሥቱ የዘረጋውን የማሻሻያ ስርአት ተከትሎ የሚደረግ ማሻሻል ደግሞ እንደተባለው መሠረታዊ ለውጥን አይጋብዝም፣ አይፈቅድምም።

ከዚህ አኳያ የእነአቢቹ(አነጋውያን) ፍላጎት ሕዝባዊ መሻቱን እና ነባራዊ ሁኔታውን ያማከለ ነው ወይ? እነ አቢቹ ሕገመንግሥቱን እንደነበረ ማስቀጠል ወይስ ማሻሻል ነው የሚፈልጉት? ማሻሻል ቢፈልጉ እንኳ በምን ዘዴ፣ መቼ እና በምን ያህል መጠን የሚለው ጥያቄ እጅግ ወሳኝ ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በትርክትም ሆነ በተግባር እንደተስተዋለው እነ አቢቹ ሕገመንግሥቱን ለአንድ ብሔር ብለው እንደማያሻሽሉት ነግረውናል፣ ምናልባት ቢያሻሽሉት እንኳ የአነጋውያንን ሰልቃጭ አዠንዳዎች ለመጨማመር በታለመ፣ ሕገመንግሥቱ እራሱ በዘረጋው ስርአት ተመስርተው እና ከምርጫው በኋላ ነው። በዚህ አግባብ ደግሞ ስርነቀል ሕገመንግሥታዊ ንቅለ ተከላ አዋልዶ የሀገሪቱን ፖለቲካ መፈወስ አይቻልም።ሕገመንግሥቱን ከነመርዙ የማስቀጠል ቁማር ያለው እዚህ ላይ ነው። ይህ ደግሞ በለውጥ ሽፋን ተረኛ ጨቋኝነትን የማዋለድ አዙሪት ነው። በመሆኑም በተለይ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው የትግል ትኩረቱ መሰባሰብ ያለበት እዚህ ቁልፍ አዠንዳ ላይ መሆን አለበት።

ለመሆኑ እነአቢቹ(አነጋውያን) ለሕገመንግሥቱ የሚሳሱለት ለምንድነው? 1ኛ ሕገመንግሥቱ ተቀናቃኞቻችንን ስለሚጎዳ ብቻ እኛን ይጠቅመናል ከሚል ስሁት አመክንዮ/fallacy፤ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛውን ከጎዳ የግድ/Necessarily የዘውግ ብሄርተኝነትን ይደጉማል ከሚል ስሌት ይመነጫል። እንዲህ ያለ እሳቤ የሚመነጨው አጠቃላይ ሀገራዊ ስእል ከማጣት እና በራስ መሻት ሰማይ ስር ከመቀንበብ ነው። ኢትዮጵዊ ብሄርተኛው ንጉሳዊ ስርአትን የታገለው እንደ ሀገር ዘመኑን የዋጀ የተሻለ ስርአት ለማዋለድ ከማለም አይደለም ወይ። በዘውጌ ብሄርተኞች ስሌት አኳያ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው ንጉሣዊ ስርአቱን ጠጋግኖ ማስቀጠል በተገባው ነበር። ምክንያቱም ዘውገኞቹ ከንጉሣዊ ስርአቱ ጀምሮ ሲታገሉ የነበሩት የተሻለ ሀገራዊ ስርአት ለማዋለድ ሳይሆን እነሱ በጨቋኝነት የፈረጁትን ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛውን ማህበራዊ መሠረት አዳክሞ ተረኛ ጨቋኝ ለመሆን እንደነበር ከወቅታዊ የፖለቲካ አቋማቸው መገንዘብ ይቻላል። ኢትዮጵዊ ብሄርተኛው ከአብዮቱ ዘመን ጀምሮ በአልነጠረ የፖለቲካ አሰላለፍ ውስጥ እራሱን ከአራጆቹ ጋር ያዋለ የመስዋእት በግ ነበር ማለት ነው።ፖለቲካችን

ከዚህ አዙሪት መውጣት አለበት። ሕገመንግሥቱ ንቅለተከላ የሚያስፈልገው በዋናነት በአጸዳደቅ ሂደቱም ሆነ በይዘቱ የቅቡልነት እጦት/legitimacy deficiency የተጋረጠበት፣ ዓለም አቀፍ የሕገመንግሥታዊነት መርህን ተከትሎ ያልጸደቀ፣ እና በይዘቱም ሀገራዊ ቃልኪዳን ከመሆን ይልቅ የአንድ ቡድን የፖለቲካ አላማ ማሳለጫ የትግል መሳሪያ በመሆኑ ነው። ሕገመንግሥቱ አማራን ወይም ኢትዮጵዊ ብሄርተኝነትን ስላገለለ ብቻ መቀየር አለበት የሚለው ሀሳብ ሕገመንግሥቱን የመቀየር መሠረታዊ ምክንያት የሚጠመዝዝ፣ ለመቀየር የሚደረገውን ትግል ማህበራዊ መሠረት የሚከፋፍል እና እዳውን ለአንድ ወገን ተጠቃሚነቱን ለሁሉም ለማላበስ የሚያደርግ ትርክት በመሆኑ መስተካከል አለበት። ሕገመንግሥቱ እንደ ሀገር የማያስቀጥለን፣ ሕዝባዊ ስርአትን የማይዘረጋ እስከሆነ ድረስ ሁላችንንም ይዞን መስመጡ አይቀርም። ስለሆነም የሕገመንግሥቱ መቀየር የኢትዮጵያውያን የሁላችን ትንሳኤ እንጂ የተወሰነ የፖለቲካ አሰላለፍ ጥቅም ጉዳይ ብቻ አይደለም። እንዲያውም ሕገመንግሥቱ ያለአግባብ አሳብጦ የሚያፈነዳው በዋናነት ተረኛውን አነጋዊነት ነው። ፊኛ የሚፈነዳው ከመጠን በላይ በመነፋት አልያም ተሸንቁሮ በመተንፈስ ነው። የፖለቲካ ሴራም እንዲሁ ነው። ወይ አሳብጦ ወይ ሸንቆሮ ነው የሚያተረሽህ።

2ተኛ የወያኔ ሕገመንግሥት በመሰልቀጥ ካልሆነም በመገንጠል የተቃኘውን የኦነጋውያን(የእነአቢቹን) ፖለቲካ ከግብ ለማድረስ ያስችላል ከሚል ስሌት የመነጨ ነው፤ በዋናነት የኢትዮጵያውያን ሁሉ ጥንተ እርስት፣ የበራራ ስልጣኔ አሻራ ያረፈበትን እና የኢትዮጵዊነት አስኳል የሆነውን የሸዋ ክፍለ ሀገርን ጨምሮ የተለጠጠ ግዛት በኦሮሚያ ክልልነት ብቻ እውቅና የሰጠ ሕገመንግሥት ከመሆኑም በላይ የመገንጠል መብትን ችሮናል ከሚል ስሌት የሚመነጭ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በዘር እና ቋንቋ ላይ ብቻ ተመስርቶ ፌደራላዊ ስርአት አዋቅሮ የዘውግ መሬት መስፈር ከነባራዊ እውነታ ጋር መቃረን ነው። ምክንያቱም በኢትዮጵያ የታሪክ ፍሰት ውስጥ የአንድ ንኡስ ማንነት ያልተቆራረጠ ዘላቂ ርስት እና ያልተዛነቀ ማንነት ኖሮ አያውቅም። ማንነታችንም ሆነ እርስታችን ሲዛነቅ እና ሲዋዋጥ የዘለቀ ነው። ሁላችንም በሁላችን ውስጥ አለን። በቀዳሚ ባለርስትነት/nativist view አመለካከት ከተቃኘን ኢትዮጵያን ጨምሮ የአለም ሀገራት በሙሉ እንደገና መዋቀር ሊኖርባቸው ነው። በቀዳሚ ርስትነት አመለካከት ከተመራን በኢትዮጵያ ሁኔታ ዋነኛ ተጎጂ የሚሆነው አነጋዊው ሰልቃጭነት ነው። ምክንያቱም እራሱ የሚያቀነቅነው ትርክት እራሱ የሰለቀጠውን ርስት እና ማንነት ሊያስተፋው ስለሚችል ነው። እንዳበጡ መገንጠል እንዳበጡ መሽሎክ አይቻልም። ምክንያቱም በእብጠቱ ልክ የመሽሎኪያው ቀዳዳው እየጠበበ ስለሚሄድ ነው። በጋራ ከበሰልንበት ቶፋ ወስጥ ንፍሮ ጨብጦ መውጣት አይቻልም። አንዱ መፍትሄ ከእውነታ ጠምዛዥ/distortive ከሆነው የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክ ላይ ከተመሠረተው የዘውጌ ፌደራሊዝም ተላቀን ነባራዊ ሁኔታውን (ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ እና መልካምድራዊ ትስስርን፣ አስተዳደር አመቺነትን ወዘተ) ያገናዘበ አወቃቀር መቀየስ ነው።

ሐ/ የቁልቁለቱ ቁልቁለት፤ ህወሀትን ከህወሀት የማዳን ዘመቻ፤

በትግራይ እየተካሄደ ያለውን ጦርነት ውስጠ ወይራነት ምንያህል በውል ተገነዘብነው? እየሆነ ያለው እንደ ዳግማዊ ኢህአዴግ/ብልጽግና ሁሉ ህወሀትን የማስወገድ ሳይሆን ህወሀትን የማዳን ተግባር መሆኑ በይደር እየተገለጠ ነው። አንድ ድርጅት የሚሞተው ተቋማዊ መዋቅሩ ከመፍረሱ በተጨማሪ በዋናን መሠረታዊ ርእዮት አለማዊ፣ መዋቅራዊ እና ስርአታዊ ቁመናው ሲሻር፣ ወይም አስቀጣይ ሲያጣ ነው። ከዚህ አኳያ አቢቹ ቅድሚያ ኢህአዴግን የሚያፈርስ አስመስሎ ከሞት አፋፍ አድኖ ብልጽግና የሚል የዳቦ ስም በማውጣት ርእዬቱን አስቀጠለው። የለውጥ መሻቱ መአበል የኢህአዴግን ርእዮት ዓለም፣ ሕገመንግሥት፣ መዋቅር እና በጥቅሉ ስርአቱን ከመሠረቱ እንዳይቀይረው በለውጥ ሽፋን ለውጡን የማምከን ሥራ እየተሠራ ቀጥሏል። ህወሀትንም በሚመለከት እየሆነ ያለው ይሄው ነው። ለብልጽግና የስልጣን ተቀናቃኝ የሚሆኑ አንጃዎችን ከውስጡ አስወግዶ የድርጅቱን መርዘኛ እሳቤ በተተኪ አንጃ አሸጋሽጎ የማስቀጠል ውስጠ ወይራ ደባ ነው በሕዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው። አጋፋሪው ኃይል አሁንም እንደ ለውጡ መባቻ ሰሞን ጁንታ ጁንታ እያለ አቢቹን ሞሽሮታል። ጁንታ ምን አንድምታ እንዳለው ግን ቆም ብሎ የጠየቀ ጥቂት ነው። አቢቹ ጁንታ ሲል ህወሀትን በአጠቃላይ አፈቅረዋለው፣ ህወሀት ያነበረውን ርእዮት፣ ስርአት፣ ሕገመንግሥት እና መዋቅር ለማስቀጠል እችል ዘንድ ከድርጅቱ ውስጥ ጥቂት አንጃዎችን ማሸጋሸግ አለብኝ እያለ ነው። ጁንታ ማለት በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለ አፈንጋጭ አንጃ እንደማለት ነው። ሕግ ማስከበር ዘመቻ የሚለው አገላለጽም ከህወሀት አንጃ መወገድ በኋላ ሊከወን የሚገባውን መሠረታዊ ፖለቲካዊ ውጤት የማዋለድን እድል አስቀድሞ የሚዘጋ ነው። ምክንያቱም ውጤቱ ከህጋዊነት አልፎ ፖለቲካዊ አንድምታ ካነበረ ወልቃይትን ጨምሮ ብዙ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ሊያገኙ ነው። ስለዚህ ወጣቱን ከማገድክ በኋላ ጉዳዩን የጁንታ እና የሕግ ጉዳይ ብቻ ታደርገዋለህ። ይሄ ▶

ከአቢቹ የሚጠበቅ ቀጣፊነት ነው።

ቀድሞውንም ቢሆን አቢቹ የህወሀት፣ የፖለቲካ ማደጎ፣ የልብ አፍቃሪ እና አስቀጣይ ነበር። በለውጡ ማግስት ለቃቅሞ ማሰር እየቻለ ህወሀት ትግራይ ከትሞ እንዲያገግም፣ መርዙን ለአዲስ ትውልድ እንዲያሰርጽ እድል ሰጠው። በዘረፉት እንዲጦሩ በመፍቀድ በሀገር የፍትህ ሚዛን ላይ ቀለደ። ሲቀጥል ወደገባበት ጦርነትም ቢሆን የህወሀት ሰይጣናዊ ተግባር ከእቅዱ ውጪ ስለሄደበት ነው እንጂ መዋጋት ፈልጎ አልነበረም። ይልቁንም ህወሀት አልጨበጥ ብላው ነው እንጂ በአብሮነት የውርሰ ጥፋቱን መርዝ በማስቀጠል ለፍሬ ለማብቃት ይፈልግ ነበር። በመሆኑም እየተካሄደ ያለው ጦርነት መንታ ኪሳራ እያስከተለ ነው። አንድም በለውጡ መባቻ ሰሞን በቀላል መስዋእትነት የወያኔን አንጃ ለፍርድ አቅርቦ የዝርፊያ ተቋሞቹን መውረስ ሲገባ፣ ይህ ባለመሆኑ አሁን ለተገባበት ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ሀገሪቱን ዳርጓታል። ሁለተኛ ዘግይቶም ቢሆን ከባድ መስዋእትነት የተከፈለለት ዘመቻ ተገቢውን ሀገራዊ ፍሬ እንዳያፈራ እና ውጤቱ ሥልጣንን የማስጠበቅ፣ የጁንታ እና የሕግ ጉዳይ ብቻ እንዲሆን እየተሠራበት ነው። ይኸውም ህወሀትን ከህወሀት አድኖ ከእነ መርዘኛ እሳቤው አሸጋሽጎ ለማስቀጠል ከታለመው የአቢቹ ስረ-መሻት ይመነጫል።

ለመሆኑ አቢቹ ለህወሀት በዚህን ያህል መጠን የሳሳለት ለምንድ ነው? 1ኛ የዘውግ ብሄርተኛውን የፖለቲካ አሰላለፍ የማስጠበቅ ውስጠ ወይራነት ነው፤ በህወሀት እና በነአቢቹ(በኦነጋውያን) ፖለቲካ ባጠቃላይ ከሥልጣን ተቀናቃኝነት ያለፈ አንዳች ልዩነት የለም። ሁሉም የሚቀዱት የኢትዮጵያዊነት ስሪትን ከሚጸየፍ የጥንተ ጠላት ተሰናሳይ ዥረት ነው። ይኸውም አውነትን አጣማሚ እና ሁሉን ለፖለቲካ መሣሪያነት ከሚሰዋ ሌኒኒስታዊ፣ ዘውጋዊ እና የጨቋኝ ተጨቋኝ ርእዮት ዓለም ነው። የአቢሲኒያን(ግዮናዊነት) ፖለቲካ አዳክሞ የማቆየት ፍላጎትን በውስጡ የጸነሰ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው። ህወሀት ከነመርዘኛ እሳቤው ከተወገደ የትግራይ እና የኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው ፖለቲካ በሕዝብ ለሕዝብ፣ በአዲስ ምእራፍ እና በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ዳግም በመሰባሰብ የፖለቲካ አሰላለፍ ለውጥ ሊፈጥር ይችላል። ይህ ደግሞ ለዘውግ ብሄርተኛው በተለይም ለኦነጋዊ የፖለቲካ አሰላለፍ ቁልፍ ማምከኛ ኃይል የሚፈጥር ነው። አቢቹ ለህወሀት ያለው ስስት በአቢሲኒያውያን መካከል የተተከለውን የጸብ ግድግዳ ለማስቀጠል እና አልፎም የትግራይን ፖለቲካ የኦነጋውያን መጋቢ አድርጎ በማቆየት በሁለት መንታ ለማትረፍ የተሰላ ነው፤ አንድም ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛውን ለማዳከም ሲሆን ሁለተኛ ኦነጋውያንን ለማፋፋት ይረዳል ከሚል እሳቤ ነው። ለዚህ ነው የአማራ ልዩ ኃይል በትግራይ በሚካሄደው ዘመቻ ዋና ተጋፋጭ ነገር ግን ከውጤቱ እንዳያተርፍ እየተሴረ ያለው። ዘመቻው ሲጀመር ጀግናው የአማራ ልዩ ኃይል ሲል የነበረው አቢቹ ቆየት ብሎ ዘመቻው ጁንታን ለሕግ ከማቅረብ የዘለለ ህወሀትን በምልአት መደምሰስም ሆነ ወልቃይትን(በአብይ አጠራር ምእራብ ትግራይ) የማስመለስ አላማ እንደሌለው የነገረን። ይህ የሚያመለክተው በአቢሲኒያውያን ፖለቲካ መካከል በወያኔ የተተከለውን የጠብ ግድግዳ ለማስቀጠል ጸብ የሚጭር እና በአንጻሩ የትግራይን እና የኦነጋውያንን የዘውግ ፖለቲካ አሰላለፍ ከጸቡ አትርፎ እንዲጸና ከመሻት ይመነጫል። ስለሆነም ጥያቄው ያለው ህወሀት መወገዱ ላይ ሳይሆን በማን፣ እንዴት፣ በምን ያህል መጠን እና መቼ ይወገድ እና ከመወገዱ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው ምን ያተርፋል የሚለው ላይ ነው።

በአቢሲኒያውያን መካከል የተተከለው የጸብ ግድግዳ በዋናነት የወልቃይት እና ራያ ጉዳይ ጋር የሚያያዝ ነው። በወልቃይት ላይ ለ27 አመት ሙሉ በወያኔ የተፈጸመው ሰቆቃ ወደር የማይገኝለት የዘር ማጥፋት እና ማጽዳት ተግባር መሆኑ ይታወቃል። ወልቃይት ከጥንት ጀምሮ በጎንደር ክፍለሀገር ስር የነበረ መሆኑም በአያሌ ማስረጃዎች የተረጋገጠ እና በትግራይ ኤሊቶች ጭምር የተመሰከረ ነው። በወልቃይት ውስጥ አማራና ትግሬን ጨምሮ ሌሎች ማንነቶችም ለዘመናት ተዋህደው መኖራቸውንም ሆነ ለወደፊቱም አብሮነታቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሕዝብ አለመኖሩም እሙን ነው። ሰንኮፉ ያለው በወያኔ እኩያ ፖለቲካዊ ውሳኔ ወልቃይትን በጉልበት ከአንዱ ቆርሶ ለአንዱ መስጠት፣ የአማራውን ዘር አጥፍቶ የሌላውን በማስፈር የሕዝብ አሰፋፈር ቅየራ ውስጥ መግባቱ ላይ ነው። በመሆኑም የወልቃይት ጉዳይ ይደር የማይባል የማንነት እና የህልውና ትግል ሲሆን ግቡም የወልቃይትን ህብራዊነት ለማስመለስ እንጂ ወያኔ በሄደበት መንገድ ለመበቀል አይደለም። ሆኖም ግን በአቢቹ በኩል የሚኖረው ምላሽ አሉታዊ መሆኑ እየታየ ነው። ምክንያቱም ወልቃይትን ሕዝብ ለሕዝብ መተማመን ላይ የተመሠረተ ፍትሀዊና ዘላቂ መፍትሔ ካገኘ በአቢሲኒያውያን መካከል የጠብ ግድግዳ የማስቀጠሉን የኦነጋውያን ስሌት ስለሚያከሽፍ ነው። የሆነው ሆኖ የወልቃይት ጉዳይ የአማራውን ብሎም የኢትዮጵያዊ ብሄርተኛውን ፖለቲካ የአላማ መዛነፍ በማያስከትል መልኩ፤ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው የዘር ፌደራሊዝምን ከመቀልበስ ትግሉ ጋር በማይቃረን መልኩ፣ ብሎም በአቢሲኒያውያን መካከል የተተከለውን የጠብ ግድግዳ አፍርሶ በአብሮነት ለመቆም በሚያስችልና፣ ወሳኝ የፖለቲካ አሰላለፍ ለውጥ በሚያስከትል መልኩ መፍትሄ እንዲያገኝ መታገል ለኢትዮጵያ ፖለቲካ በጣም ወሳኝ አንድምታ ይኖረዋል።

2ተኛ የሽግግር ፍትህን አድበስብሶ ለአስቀጣይነት ፖለቲካ መሰዋት፤ ለውጡ ሊያሳካቸው ከሚገቡ አንኳር ትሩፋቶች አንዱ የሽግግር ፍትህን ማስፈን ነው። በተቃራኒው እየሆነ ያለው ግን የሀገሪቱን የፍትህ ሚዛን ያዛባ፣ ማልያ ቀያሪ ወንጀለኞችን ለዳግም ሹመት እና ዘረፋ እድል የሰጠ ከባድ የታሪክ ጠባሳ የሚያሳርፍ ተግባር ነው። የሽግግር ፍትህ አጠቃላይ ኢህአዴግን በሚመለከት የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችን መውረስ/nationalize ማድረግን፣ ወንጀለኞችን በሚገባ አንጥሮ እንደየጥፋት መጠኑ በይቅርታ፣ ከሲቪል መብት መታገድ እና ለቅጣት መዳረግ እጅግ ወሳኝ ነው። ነገር ግን በዳግማዊ ኢህአዴግ በኩል “በለውጥ” ሂደቱ የሽግግር ፍትህን ማንበር እራስን እንደማጥፋት ያለ ውጤት ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋት አለ። አንደኛ ከላይ የተብራራውን የኦነጋውያን እና የወያኔ ተሰናሳይ የዘውግ ፖለቲካ አስቀጣይነት ከመዋቅር መንግሎ ሊያዳክመው እና ቅራኔ ውስጥ ሊከተው ይችላል ከሚል ስጋት የሚመነጭ ሲሆን፤ ሁለተኛ ተሻጋሻጊዎቹን(ተደማሪዎቹን) ኦህዴድ እና ብአዴንን በሽግግር ፍትህ ቁና ለመስፈር መሞከር ተደማሪዎች በለውጡ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ይህ ከሆነ ደግሞ የብልጽግና እና የአቢቹ የእርካብ እና መንበር መሰላል መነቃቀል ይጀምራል። ስለዚህ መፍትሄው ህወሀትን ጨምሮ አጠቃላይ ኢህአዴግን በሽግግር ፍትህ ወንፊት ከማበጠር ነጻ የማድረግ እና አለባብሶ የማረስ አማራጭ ውስጥ መግባት ሆነ። ይህ ደግሞ አለባብሰው ቢያርሱ በአረም... የመመላለስ ቁልቁለት ውስጥ ዘፍቆናል።

መቋጫ፤

አሁን ላለንበት አዘቅት የዳረገን ስርነቀል አብዮት በማይገባው ስርአት ላይ አብዮት ማድረጋችን እና በአንጻሩ ስርነቀል አብዮት የሚያስፈልገውን የወያኔ ስርአት አለባብሰን ለማስቀጠል መዋተታችን ነው። ከንጉሡ ስርአት ወርሰን ማስቀጠል የሚገባንን ቱባ፣ መሠረታዊ የኢትዮጵያዊነት ውሃልክ የሆኑ፣ እና የኢትዮጵያዊ ብሄርተኛው እሴቶችን እና ተቋማትን አውድመን ስናበቃ፤ በአሁን ወቅት ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን የሸረሸ እና ያዋረደ የወያኔ ስርአትን በአንጻሩ ስርነቀል ለውጥ እንዳይፈጸምበት በለውጥ ሽፋን ለውጥን የሚከላከል ስርአት ወደማንበሩ እየተንደረደርን ነው። መፍትሄው በፖለቲካ ሽግግራችን ውስጥ መንቀል እና ማስቀጠል ያለብንን አንኳር እሴት አንጥሮ ሲያበቁ በመልካም እሴቶቻችን ላይ የተመሠረተ ዘለቄታዊ ሕዝባዊ ስርአት ማዋለድ እና እራስን መሆን ነው።

# ፍርድ ቤቱ ሆይ !

## አስካለ ደምሌ፤ ከቃሊቲ ወህኒ ቤት (የፖለቲካ እስረኛ)



### መነሻ

በእነ እስክንድር ነጋ መዝገብ በሽብር ወንጀል ተከስሸ ያለ አንዳች ጥፋት ቃሊቲ ወህኒ ቤት እገኛለሁ። ችሎት በምንቀርብበት ጊዜ ጉዳያችንን ዘርዝረን እንድናስረዳ በቂ ጊዜ አልተሰጠንም። ንግግሮቻችን በሽራፊ ደቂቃዎች የተገደቡ ናቸው። በመሆኑም ለፍርድ ቤቱም ሆነ ለሰፊው ሕዝብ ይደርስ ዘንድ ይህንን መጣጥፍ አዘጋጀሁ።

"መንግሥት ላይ ጫና መፍጠር እና የእርስ በእርስ ግጭት ማስነሳት" በሚል ክስ ተመስርቶብኝ እስር ቤት ሆኜ ጉዳዬን እየተከታተልኩኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ለመታሰሬ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከመከሰቱ በፊት፡-

1. በመንግሥት ተቋም ውስጥ በምሠራበት ወቅት በእያንዳንዱ እንቅስቃሴዬ ልክ መንግሥታዊ የስለላ አባላትን በመመደብ፣ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የብልጽግና ፓርቲ አመራሮች "መንግሥት ደሞዝ እየከፈለሽ በባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ መሳተፍ የለብሽም" ብለው በአካል እና በስልክ ተፅዕኖ ሲፈጥሩብኝ ነበር።
2. የፖለቲካ ተሳትፎዬን ብቻ በማየት በርቀት መከታተያ (GPS) አማካኝነት ሲሰልሉኝ ቆይተዋል። ግንቦት 21 ቀን 2012 ዓ.ም ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ስልክ ደውለው አስፈራርተውኛል። ይህንን ፍርድ ቤቱ ሊረዳው ይገባል። ለክሱ ሰበብ የሆነው ክስተት ከተፈጠረ ከ42 ቀናት በኋላም ያለ አንዳች ማስረጃ አስረውኛል። እነኝሁ ሰላዮች በአካል አግኝተው ፖለቲካዊ አቋሜን እንድቀይር ጠይቀውኛል። ይህንን ካደረግኩ የጋራ መኖሪያ ቤት እንደሚሰጠኝና የኦሕዴድ/ብልፅግና አመራር እንደምሆን ነግረውኛል። ይህን ካልፈለግኩ ከሀገር ወጥቼ መኖር የምችልበትን ዕድል እንደሚያመቻቹም ገልፀውልኛል። እነኝህን መደለያዎች ባለመቀበሌና አቋሜን ባለመቀየሬ ወደ እስር ቤት የተወረወርኩ መሆኑን ሕዝብም ሆነ ፍርድ ቤቱ ሊያውቁት ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ የደህንነት መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች በሄድኩበት እየተከታተሉ ፎቶ ግራፍ ሲያነሱኝ ነበር።
3. አዲስ አበባ ኮልፌ ቃራኒዮ ክፍለ ከተማ ዓለም ባንክ ፉኑኤል በሚባል ቦታ ለተፈናቀሉ ህዝቦች ከባልደራስ የተደረገውን ድጋፍ ልናደርስ ቦታው ላይ በተገኘንበት ወቅት እኔን ጨምሮ ብዛት ባላቸው የመንግሥት የፀጥታ አካላት ተረጂዎችና የባልደራስ አመራሮች ታግተን ቆይተናል። ካራ ፖሊስ ጣቢያ ታስረን ከሰዓታት በኋላ እርዳታውን ሳናከፋፍል ከእገታው ተለቀን መመለሳችን ወትሮም ለክስ ሰበብ እየተፈለገልን እንደነበር አመላካች ነው።

በለገሀር የይሁዳ አንበሳ ሃውልት እና ዙርያውን ለማፅዳት፣ ችግኝ ለመትከል እና የዘርዓይ ደረስን 82ኛ ዓመት ዝክረ በዓል በማክበር ላይ እያለን ፕሮግራሙን ሳንጨርስ እኔን ጨምሮ የባልደራስ ከፍተኛ አመራሮች እና ደጋፊዎችን ብዛት ያላቸው የመንግሥት ፖሊሶች አስቆሙን። ቀጥሎም ወደ ለገሀር ፖሊስ ጣቢያ ወስደውን ካገቱን በኋላ ለቀውናል።

በባልደራስ 6ኪሎ ከተፈሪ መኮንን ከፍ ብሎ የሚገኘው ዋና ጽ/ቤት ውስጥ ሥራ ላይ እያለን የፌዴራል ፖሊሶች መጥተው ጠመንጃ ደቀኑብን። በማስፈራራት አቋሜን ለማስቀየር፣ የፖለቲካ ተሳትፎዬን ለመግታት ጥረት ሲደረግ እንደ ነበረና ይህ እስርም የዛው አካል መሆኑ ይታወቅ።

ፍርድ ቤቱ ሆይ በቁጥጥር ስር ከዋልኩኝ በኋላም የፌዴራል ወንጀል ምርመራ ቢሮ (ማዕከላዊ) እያለሁኝ ሁሉም ተጠርጣሪ ተቆጥሮ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ሰዓት እላፊ መስኮት ከተው ለምስክሮች ሲያስጠኑኝ፣ የተለያዩ ማስፈራራቶች ሲደርስብን እንደ ነበረ እና በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደረግኩኝ መሆኑ ይታወቅልኝ።

4. በምርመራ ላይ በነሐሴ 5 ቀን 2012 ዓ.ም በመርማሪው ስጠየቅ ከነበሩት ውስጥ፤ "የአፄ ምኒልክ ሃውልት እንዳይፈርስ የአዲስ አበባን ሕዝብ አደራጅተሽ ታግለሻል፣ መንግሥት ደሞዝ እየከፈለሽ ለምን የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር መሆን አስፈለገ፣ አዲስ አበባ የነዋሪዎቿ ነች በማለት በአስሩ (10) ክፍለ ከተማ ወጣቶችን ወይም ህዝቦችን ለባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ስታደራጅ ነበረ" በማለት መርምሮኛል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጉዳዩ የፖለቲካ እንጂ የሕግ እንዳልሆነ ነው።
5. በአዲስ አበባ የሥራ ዕድል ፈጠራን አስመልክቶ እና ለአዲስ አበባ የመጣ የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ብሔርን ያማከለ ስለ ነበር ለሁሉም ብሔር እድሉ መድረስ አለበት በማለት የበኩሌን ድርሻ ተወጥቻለሁኝ። ይህም ለመታሰሬ አንድ ምክንያት ነው፡፡
6. በአዲስ አበባ ውስጥ በብዙ ወረዳዎች ላይ የቀበሌ መታወቂያ ሕጋዊ ሂደቶችን ሳይከተል ማለትም መሸኛ ሳይመጣ፣ በሀሰተኛ የድንች ማህተም በወረዳዎች ግቢ ውስጥ መዘጋጀቱ እየታወቀ፣ ያለ ባለቤት ፍቃድ በሰው ቤት ቁጥር መታወቂያ ለኦሮሚኛ ተናጋሪዎች ብቻ እየታደለ፣ ህጋዊ መስፈርቶችን አሟልተው ከሌላ የኢትዮጵያ ጫፍ ለሚመጡ እየተከለከለ ብሎም መሸኛቸው ላይ ከጀርባ ከ6 ወር በኋላ ነው የምትስተናገዱት መባለቸውን፣ በጋሃድ ስለተቃወምኩኝ ብቻ ሳይሆን ስለ ታገልኩኝ ሚዛናዊ አገልግሎት መኖር አለበት ስላልኩኝ መታሰሬ ይታወቅ።
7. በአዲስ አበባ የወረዳ ሥራ አስፈፃሚዎች ላይ መታወቂያ በዜሮ ዜሮ (00) ኮድ እንድያወጡ በሥም ዝርዝር ከበላይ አካል መርተውላቸው እሱንም ወደ መታወቂያ ክፍል እንዲያስተላልፉ ጫና ሲደረግባቸው ስለነበረ ይህ አግባብ አለመሆኑን ተቃውሜያለሁ። ታግያለሁ። የእስሬ ምክንያትም ይኸው ነው።
8. ያለአንዳች ህጋዊ እና አስተዳደራዊ ምክንያት ከኦዴፓ (የብልጽግና ፓርቲ ኦሮሚያ ቅንጫፍ አባላት) ውጪ የሆኑትን ዜጎች (ብሔረሰቦች) ከሥራ ገበታቸው ሲባረሩ፣ ከአመራርነት ዝቅ ሲደረጉ በማየቴ እና በመታገሌ የደረሰብኝ እንግልት እና እስር ነው።
9. በመንግሥት መሥሪያ ቤት ብሄርን የማጣራት ሥራ ስለ ተጀመረ ለምን አስፈለገ?፣ የሚል ተቃውሞ በማስነሳቴ ምክንያት የመጣ እስር

እንጂ እንደ ተባለው ወንጀል ሰርቼ እንዳልሆነ ፍ/ቤቱ እንዲገነዘብልኝ እጠይቃለሁ፡፡

10. የብልጽግና ፓርቲ ኦሮሚያ ቅርንጫፍ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ አመራሮች በሥራ ልምድ፣ በትምህርት ዝግጅትና በመፈፀም ብቃት የተሻለ እያለ በብሔር ተረኛ ነኝ ባዮች ሲመዳደቡ እና እነዚሁ አመራሮች ደግሞ በዚሁ ተረኝነት ስሜት ሌሎችን በትምህርት ዝግጅት እና ልምድ ያነሱበትን ለመመደብ ሲንቀሳቀሱ አይቼ ታግያለሁኝ። ወደ ፊትም እታገላለሁ። እስሩም ከዚሁ የመነጨ መሆኑ ይታወቅ።

11. ከ1997 ዓ.ም. እና 2005 ዓ.ም. የጋራ መኖሪያ ቤት የተመዘገቡትን ባለ እድሎችን አስመልክቶ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ በእጣ አወጣጡ፣ ቅድመ ቁጠባ ቆጥቦ ጨርሶ እጣ ውስጥ ያለ መካተታቸውን አስመልክቶ፣ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ ዕጣ ውስጥ ያለው መግባታቸው፣ ቤቱ የደረሳቸው ደግሞ ቤቱን አለመረከባቸውን፣ ሳይቆጥቡ የተሰጣቸውን እና ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ ለአንድ ብሔር ብቻ መታደላቸውን አስመልክቶ ፓርቲው የማህበረሰቡን ቅሬታ ለመቀበል በማህበራዊ ሚዲያው የግል ስልኬን ለጥፎ ስለ ነበር የመንግሥት አካላት ደውለው "የተለጠፈውን ስልክ አንሺ" እያሉ ሲዝቱብኝ ነበር፣ ይህን አስመልክቶ ብዙ ቅሬታዎችን አስተናግደናል። እኔም ይህንን ድርጊት በመቃወሜ የመጣ እስር እንጂ እንደ ተባለው ወንጀል ሰርቼ እንዳልሆነ ፍርድ ቤቱ ሆይ እንድትረዳልኝ እጠይቃለሁ።

12. እኔን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞችን ብልግጽና ፓርቲን ትቀበላላችሁ አትቀበሉም በማለት የተለያዩ ማስገደዶች ሲደርሱ አይቼ ለምን በማለት ስለ ተቃወምኩኝ የመጣ እስር እንጂ ወንጀል አልሠራሁም።

አዲስ አበባ የምትተዳደረው በቻርተር ሆኖ ሳለ በቻርተሩ ላይ የሥራ ቋንቋ አማርኛ መሆኑን በግልፅ ደንግጎ እያለ በ2011 ዓ.ም "እኔ የምሠራበት መሥሪያቤት አዲስ ብድር እና ቁጠባ ተቋም" (አማ) ለክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ አውጥቶ ማስታወቂያ ላይ ኦሮምኛ መናገር መፃፍ የሚችል የሚል መስፈርት አመጣ። ይህንን በመቃወሜም ታስሬያለሁ።

13. ሚያዚያ 27 ቀን 2012 ዓ.ም የአርበኞች የድል ቀን ሲከበር የባልደራስ ለእውነተና ዴሞክራሲ ፓርቲ የሰማዕታት ሃውልት ላይ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች እኔን ጨምሮ የአበባ ጉንጉን አስቀምጠን ስለ ነበር ይህ ሁኔታ በማህበራዊ ሚዲያ ፎቶ ተሰራጭቶ ነበር። የመንግሥት አመራሮች ይህን ፎቶ በማየት ይህንን ድርጊት አቁሚ ብለው ከፓርቲው ጋር ያለኝን ግንኙነት ለማስቆም ብዙ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ የሀሰት ክሱም የመነጨው ከዚህ ነው።

14. በኢትዮጵያ ቤተመንግሥት መግቢያ በር ላይ የተገነቡት የፒኮክ ምልክቶች የሀገራችንን ምልክት የማይገልፁ በመሆናቸው ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ አግባብ አይደለም በማለት የተቃውሞ ፊርማ ማሰባሰቡ ይታወቃል፡፡ እኔም ከፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ጋር በመሆን "እኔ ብሄራዊ ምልክቴ አንበሳ እንጂ ፒኮክ አይወክለኝም" የሚል ቪዲዮ በማህበራዊ ሚዲያ አሰራጭቻለሁ፡፡ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ይህንን ቪዲዮ በማየት ከፍተኛ ተፅዕኖ ከመፍጠራቸውም በዘለለ ለእስር ዳርጎኛል፡፡

15. አዲስ አበባ ሲቪል ሰርቪስ 2012 ዓ.ም በወጣው ክፍት የሥራ መደብ ላይ ምዝገባውም ቅጥሩም ብሄር ብሔረሶችን የሚወክል አይደለም፣ አንድ ብሔር ማለትም ኦሮምኛ ተናጋሪዎችን ብቻ የሚወክል ነው በማለት መቃወሜ ለእስር እና ለተለያዩ የመብት ጥሰቶች ያጋለጠኝ መሆኑን ፍ/ቤቱን ማስገንዘብ እፈልጋለሁ፡፡

16. አዲስ አበባ የነዋሪዎቿ ነች፣ ማንኛውም ዜጋ መጤም ሰፋሪም ሊባል አይገባም በማለቴ የመጣ እስር ነው። ክሱ በራሱ ማንነትን መሠረት ያደረገ፣ የመናገር፣ የመቃወም፣ የመደራጀት፣ ህገ መንግስታዊ መብትን የሚጥስ ብቻ ሳሆን አማራ እና የደቡብ ተወላጆችን (የጋሞ ተወላጅ) በጋራ ማደራጀት የሚለው ክስ በእራሱ ልዩነትን የሚያሰፋ ነው። ሁለቱ ሕዝቦች በአንድ ላይ ቢደራጁም የሚያለሙ እንጂ የሚያጠፉ አይደሉም። ስለዚህ ክሱ መሠረተ ቢስ ነውና ሊዘጋ ይገባል፡፡

17. አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ቀለም ያላቸውን አልባሳት፤ የአጼ ምኒልክ ምስል ያላቸው ቲሸርቶችን በመሥሪያ ቤት አካባቢ ስለብስ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀዩ አልፀደቀም በማለት እና ቲሸርቱ ላይ ያላቸው እይታ መጥፎ በመሆኑ ለመታሰሬ ምክንያት ሆኗል።

18. የብልጽግና ፓርቲ አመራሮች በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት ማህበረሰቡ ውስጥ ገብተው 1 ለ 5 ሲያደራጁ ለማህበረሰቡም ሆነ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ሰራተኞች ከፍተኛ አደጋ ያጋልጠናል በማለት ስለ ተቃወምኩኝ የታሰርኩ መሆኔን ፍ/ቤት እንዲገነዘብልኝ እፈልጋለሁ።

19. በሀገሪቷ በአጠቃላይ እንደ ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ካለን ብዙ ሃሳቦች በጥቂቱ የንፁሃን ዜጎች ሞት፣ መፈናቀል፣ የዘር ማጥፋት፣ የንብረት መውደም፣ የኃይማኖት ተቋማት ማለትም የመስጊድ፣ቤተክርስቲያን እና ሌሎችም መቃጠል፣ መፍረስ፣ መዋረድ የለባቸውም በማለት ስለ ተቃወምን እና ስላወገዝን ለእስር የተዳረግን መሆናችን ግልፅ ነው። መንግሥት አቻ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በተለያዩ ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ጠርቶ ሲያወያይ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲን ግን አንድም ውይይት ላይ አላሳተፈውም። ይህ ደግሞ የሚያመላክተው ካለን ሕዝባዊ ቅቡልነት የተነሳ መንግሥት በጥላቻ የሚመለከተን መሆኑን ነው። ፍ/ቤቱም ሆነ መንግሥት እንዲረዳ የምንፈልገው ሌላኛው ጉዳይ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ሰው በአመለካከቱ ልዩነት ምክንያት፣ በብሄሩ ምክንያት፣ በኃይማኖቱ ምክንያት፣ በፖለቲካ አቋሙ ምክንያት ለእስር እና ለተለያዩ መገለሎች መዳረግ የለበትም የሚል ነው፡፡

20. የመንግሥት አካላት የፖለቲካ ተሳትፎዬን በማወቅ የእጅ ስልኬን ቀድመው በመጥለፍ ሲከታተሉኝ ነበር። አሁንም በእጃቸው ላይ የሚገኘውን ስልኬን የኢንተርኔትና የስልክ ጥሪ እየተጠቀሙበት ነው። የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የመሠረተብኝ ክስ አንድም ለመጠርጠር እንኳን የሚያበቃኝ በሌለበት፣ አንድም አካል ለህገ ወጥ ዓላማ ማደራጀቴን ማስረጃ ባልቀረበበት ነው።

21. የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ የመመስረቻ ጉባኤ ላይ መስራች አባል ስለሆንኩኝ፣ በጉባኤው ላይ መገኘቴን ከማህበራዊ ሚዲያ መረጃ በማየት፣ የመንግሥት ደህንነት አካላት ከፍተኛ ክትትል ከማድረግም ያለፈ የፓርቲው አባልነቴን እንዳቆም ጥረት አድርገዋል። የምሠራበት ተቋም ማለትም አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም (አማ) የሠራተኞችን መብት የሚጥስ፣ጉልበት (በብዙ ኃይል የሚሠራን ሥራ አንድ ሰው ላይ በመጫን) ሠራተኞች ሲቀጠሩ የሥራ ድርሻ የማይሰጥበት፣ የሠራተኛ ጥቅማ ጥቅም የማይከበርበት፣ ሠራተኛ ከሥራ ሲለቅ የሠራውን ሥራ በሥራ ልምዱ ላይ በዝርዝር አለማስቀመጥ፣ እውቀት፣ ልምድና ትምህርት ዝግጅት የተሻለ እያለ ከዚህ ያነሱትን ማስቀደም ስለሌለ፤ ይህ መሆን የለበትም መሥሪያ ቤቱ የሠራተኛ ደም መጣጭ ነው በማለት ስለ ተቃወምኩኝ የታሠርኩ መሆኔን ፍ/ቤቱን ማሳወቅ እፈልጋለሁ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት ለእስር ካጋለጡኝ ጉዳዮች መካከል ከብዙ በጥቂቱ ናቸው። በመሆኑም የግል ጥቅሜን ባለማስቀደም፤ ለሀገር ህልውና በመታገሌ የመጣ ክስ መሆኑን አውቆ ፍርድ ቤቱ ውድቅ እንዲያደርግልኝ እጠይቃለሁ። ስለ እውነት ብላችሁ ከእስር እንድንፈታ በልዩ ልዩ መንገዶች በአሳሪዎች ላይ ጫና እየፈጠራችሁ ላላችሁ ሰዎች ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

# የኢትዮ ቴሌኮም ሽያጭ ጥቅምና ጉዳት (ሙያዊ ቅኝት)

(ሳመንጉሥ ጥላሁን)

## አፄ ምኒልክና የመጀመሪያው የስልክ ግንኙነት

ኢትዮጵያ፣በ1886ዓ.ም፣በታላቁ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት፣ የመጀመሪያውን የ477 ኪ.ሜ የስልክ መሥመር ዘርግታ፣“ጤና ይስጥልኝ ዐዲስ!! ጤና ይስጥልኝ ሐረር!!” ካስባለች፣126 ዓመታት ተቆጠሩ። አፄ ምኒሊክ፣ሀገሪቷን ያስተዳድሩ በነበሩበት ዘመን ያስገቧቸውን፣ዘመናዊ አሠራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ብዛት ስናይ፣አፄ ምኒልክ፣“የሥልጣኔ ማግኔት ነበሩ!!” ለማለት እንችላለን።

## አፄ ኃይለሥላሴና የቴሌኮሙኒኬሽን እድገት ኹኔታ

የቴሌፎን ቴክኖሎጂ ወደ ኢትጵያ የገባው፣በ1886 ዓ.ም በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው:: የምኒሊክን ፈለግ የተከተሉት አፄ ኃይለሥላሴም፣ኢትዮጵያን፣በኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ እድገት እንድታሳይ፣ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ከ1903 ዓ.ም ጀምሮ፣በተቋም ደረጃ፣የፖስታ፣ የቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር (ፖቴቴ) እየተባለ ይጠራ የነበረውን፣የቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤት፣በ1945 ዓ.ም፣በአዋጅ፣"የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድ (IBTE)" ወደሚል አዲስ ስም በመቀየር፣ኹለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፣የሀገሪቱን የቴሌኮሙኒኬሽን አቅም በእጥፍ በማሳደግ፣በዐዲስ አበባ ብቻ፣ሦስት ሺህ የስልክ ጥሪዎችን የሚያስተናግዱ የአውቶማቲክ ማዞሪያዎች በመትከል፣ሥራ ላይ ለማዋል ችለዋል። ይኽ ፈጣን እድገት ሊመዘገብ የቻለው፣የመጀመሪያውን የምሥረታ ዓመት፣የቴክኒክ ባለሞያዎችን እንዲኹም ብቃት ያለው የሥራ አመራርን ሊሰጡ የሚችሉ ባለሞያዎችን ለማፍራት የሚያስችሉ፣ተመጣጣኝ ሥልጠናዎች በመሰጠታቸው ነበር።

የደርግ መንግሥትና የቴሌኮሙኒኬሽን ማናጅመንት

የደርግ መንግሥት፣የተቋሙን ስም፣ኹለት ጊዜ የቀያየረ ቢኾንም፣በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን፣ ደረጃ በደረጃ ይካኼድ የነበረውን፣የቴሌኮሙኒኬሽን እድገት ለማስቀጠል የሚያስችለውን ቢሮክራሲያዊ አሠራር፣አላፈረሰም። የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን (ኢ.ቴ.ኮ) ፣ሀገሪቷ ባፈራቻቸው፣ከፍተኛ ብቃት ባላቸው ባለሞያዎች፣ኢንጅነሮችና ማናጀሮች እንዲመራ አድርጓል። በደርግ ዘመን፣ ልክ እንደ ኢ.ቴ.ኮ ኹሉ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፣ንግድ ባንክ ፣ ንግድ መርከብ፣መድን ድርጅት፣መብራት ኃይል፣አውራ ጎዳና እንዲኹም በዐሥር ዘርፍ ተከፍለው የነበሩ የኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽኖች ይመሩ የነበሩት፣የሞያ ነፃነታቸው በተከበረላቸው፣የማናጅመንት አካላት ነበር። ደርግ፣ምንም ዓይነት የምዕራባውያን የፋይናንስ ብድርም ኾነ እርዳታን የማያገኝ መንግሥት የነበረ ቢኾንም፣ወሳኝ የኾኑትን የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ተቋማት፣አንፃራዊ በኾነ መልኩ ከፖለቲካ ነፃ በማድረጉ፣የሀገሪቷን ከፖለቲካ ውጪ የኾነውን አስተዳደራዊ አቅሟን፣አሟጦ ለመጠቀም አስችሎታል። ይኽ እርምጃው፣በኢንዱስትሪውም ኾነ አገልግሎት ሰጪ ተቋሟት ላይ፣በውጪ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት ይፈጠሩ የነበሩ ችግሮችን፣በሀገር ውስጥ አቅም ለማካካስ እንዲያስችለው፣ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጎለታል።

## የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥትና የቴሌኮሙኒኬሽን ማናጅመንት

ደርግን ተክቶ ሥልጣን ላይ የወጣው፣የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት፣በአንፃሩ፣የመጀመሪያ ሥራው ያደረገው፣በደርግ ዘመን፣የሞያ ነፃነት የነበራቸውን መንግሥታዊ ተቋማትን በማፈራረስ፣ድርጅቶቹን የሚመሩትን ቢሮክራቶች፣መበታተን ነበር። ለዚኽም ጥሩ ምሳሌ የሚኾነው፣በአንድ ሌሊትና በአንድ ፊርማ፣ዐሥሩን የኢንዱስትሪ ዘርፎች ይመሩ የነበሩትን ኮርፖሬሽኖች አፍርሶ፣ከፍተኛ ባለሞያዎችን መበተኑ ነበር። በኮንስትራክሽን ዘርፉም፣የኢትዮጵያ ሕንፃ ኮንስትራክሽንን:: ከኢንዱስትሪውም ወጣ ብለን ብናይ፣ባለሞያ

ጠሉ ኢሕአዴግ፣የዐዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ መምህራንን፣ከሥራ ለማባረር የወሰደውን ተመሳሳይ እርምጃ ማስታወስ እንችላለን።

ከመፈራረስ የተረፉትንም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽንና የኢትዮጵያ አየር መንገድን የመሳሰሉ፣ የሀገሪቱ ትልልቅ ተቋማት ከፍተኛ የማናጅመንት አመራር ቦታዎችን እንዲኹ፣የብሔር ፖለቲካን ለሚያራምዱ እንደነ አቶ ስዩ አብርሃና ዶ/ር አብዱልመጂድ ሁሴንን ለመሳሰሉ ሹማምንቶች በማስተላለፍ፣የሀገሪቱን ዋና ዋና ተቋማት የሥራ አመራር፣ቀድሞ ከነበሩበት፣ ከፖለቲካ ነፃ ሞያዊ አስተዳደር ወደ ፖለቲካዊ ቅኝት ያለው አስተዳደር እንዲያሽቆለቁሉ አደረጉ።

ከደርግ በተለየ፣ወያኔ ኢሕአዲግ፣ የምዕራባውያንን ድጋፍና አዎንታ ያልተለየው መንግሥት ስለነበር፣የወርልድ ባንክንና የአይ.ኤም.ኤፍን እንዲኹም የምዕራባውያን ሀገራትን ብድርና እርጥባን፣በቀላሉ ያገኝ ነበር። ይኽ የውጪ ብድርና የገንዘብ እርዳታ፣ከፖለቲካ ነፃ የነበረውን ቢሮክራሲ በማፈራረሱ ምክንያት፣እየተከሰተ የነበረውን፣ዘለቄታዊ ገጽታ ያለው የኢኮኖሚክና ማህበራዊ አደጋ ማየት እንዲሳነው ወይም እያወቀም ቢኾን፣ከቁብ እንዳይቆጥረው አድርጎታል። ይኽ፣የወያኔ ኢሕአዲግ ባለሞያ ጠል እርምጃው፣እጥፍ ድርብ ችግሮችን እየወለደ፣ለ30 ዓመታት ሲንከባለል ቆይቶ፣በአኹኑ ሰዓት፣እንደ የኢትዮጵያ መብራት ኃይልና የኢትዮጵያ መንገድ ባለሥልጣንን የመሳሰሉ የመንግሥት ተቋማትን፣ወደ 600 መቶ ቢሊዮን ብር የሚጠጋ እዳ ባለቤት አድርጓቸዋል።

የኢትዮጵያቴሌኮሙኒኬሽንኮርፖሬሽን፣በወያኔ ኢሕአዲግ መንግሥት መስተዳደር ከጀመረበት ከ1983 ጀምሮ፣የተጓዘበትን መንገድ ስንዳስስ፣የእነ ዶ/ር አብዱልመጂድ ሁሴን የኮርፖሬሽኑን የከፍተኛ አመራር ቦታ ሹመት ተከትሎ፣ቀስ በቀስ፣አጠቃላይ ማናጅመንቱን፣በተለያዩ የብሔር የፖለቲካ ሹመኞች በመለወጡ፣መሥሪያ ቤቱ፣ለከፍተኛ የአሠራር ችግሮችና እንቅፋቶች እንዲጋለጥ መደረጉን፣እንገነዘባለን። የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ፣እንደሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ከአጠቃላዩ ሕዝብ የቀን ተቀን እይታ ውጪ፣እንዲኹም ከሌሎች ሀገራት የቴሌኮሙኒኬሽን እድገትና አጠቃቀም አንፃራዊ እይታ ውጪ ሊኾን ስለማይችል፣ወያኔ ኢሕአዲግ፣ውሎ አድሮም ቢኾን፣መሥሪያ ቤቱ ላይ ያንሰራፋውን፣ለሥራና እድገት ማነቆ የኾነውን፣ፖለቲካዊ ገጽታ ያለውን ማናጅመንት ለመቀየር፣እንዲያስብበት አስገድዶታል።

በዚኽም መሠረት፣ከፍተኛውን የማናጅመንት የሥራ ቦታ፣በ1995 ዓ.ም፣ከዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመጡ መምህራን፣እንዲያዝ አድርጓል። ዐዲሶቹ የማናጅመንት አባላት፣በቴሌኮም ኢንዱስትሪው የነበራቸው ልምድ አነስተኛ በመኾኑ፣ከነባር ኢንጅነሮችና ኤክስፐርቶች ጋር፣ አንዳንድ አለመግባባቶችና ቅራኔ ቢፈጥሩም፣እነዚኽ መምህራን፣የራሳቸው የኾነ፣የለውጥ ዕቅድ የነበራቸው ነበሩ። የቴሌኮም መሠረተ ልማትን ከማስፋፋት ባሻገር፣በተለይ የሀገሪቱን የቴሌኮም አቅም ለማሳደግ፣ወሳኝ የኾነውን የሰው ኃይል ለማፍራት፣ፈጣንና ተግባራዊ ሥራዎችን ለማከናወንም ችለውም ነበር። ለዚኽም፣እንደ ምሳሌ ሊወሰድ የሚችለው፣የቴሌኮሙኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት(ICTIT) እየተባለ ይጠራ የነበረውን፣ለማቋቋም ያደረጉት ተግባራዊ ጥረት ነው። ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን፣የኤም አይቲ ዶክቶራል ዲግሪ ተመራቂ ኢትዮጵያውያዊ መምህራንን ያካተተው ይኽ ተቋም፣ኢንፎርሜሽን ሳይንስ፣ቴሌኮም ኢንጂነሪንግና ቴሌኮም ማናጅመንትን የመሳሰሉ ዲፓርትመንቶችን በመክፈት፣በማስተርስ ዲግሪ ደረጃ፣ለወጣት ተተኪ የተቋሙ ሠራተኞች እንዲኹም ከተቋሙ ውጪ ላሉ፣በቴሌኮም ዘርፍ ሞያ ለመቀጠል ለሚፈልጉ፣ብሩህ አእምሮ ላላቸው ተወዳዳሪ ተማሪዎች፣በክፍያና በስኮላርሺፕ መልክ፣የትምህርት እድል እንዲያገኙ ያደረጉት ተግባራዊ ሥራ፣የሚጠቀስ ነው። ይኹንና፣ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት፣ከፖለቲካ ነፃ የኾነ፣በፕሮፌሽናሎች የሚመራ፣ቢሮክራሲን አጥብቆ የመጥላት አባዜው የሚለቀው ስላልነበረ፣እነዚኽ ከዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጡ የማናጅመንት አመራሮች፣ሦስት ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው፣በሙስና እንዲከሰሱ አድርጎ፣ ወደ ወኽኒ ቤት አወረዳቸው። የእነርሱን ወደ ወይኽኒ ቤት መውረድ ተከትሎም፣የሃገሪቷን የቴሌኮም ዘርፍ የሰው ኃይል አቅም ለማሳደግ እንዲረዳ ያቋቋሙትንም ኢንስቲትዩት ዘጋው። አጠቃላይ የማናጅመንት ቦታውን፣በአውራ ካድሬዎች መልሶ እንዲያዝ አደረገ።

## በፋይበር ብሮድባንድ ኢንተርኔት ኮኔክሽን ለማግኘት የተደረገው ስምምነት

እነዚያ ካድሬ ማናጀሮች፣ሥልጣናቸውን እንደተረከቡ፣ከ800 ሜጋ ባይት የማይበልጠውን፣ በዋናነት ከሳተላይት ሊንክ ይገኝ የነበረውን፣የሀገሪቷን የኢንተርኔት አቅም ለማሳደግ፣ የ47ሚሊዮን ዶላር ስምምነት፣ለምሥራቅ አፍሪካ የመጀመሪያውን ኢንተርናሽናል ሰብማሪን የብሮድባንድ ኬብል ከዘረጋው፣ከሲኮም (SEACOM) ኩባንያ ጋር ተፈራረሙ። በስምምነቱም፣ ሲኮም፣ለገበያ ካቀረበው 2.3 ቴራ ባይት ኢንተርናሽናል ብሮድባንድ ሊንክ ላይ፣0.25% ማለትም 2.5 ጊጋ ባይት ኢንተርኔት ኮኔክሽን፣ጅቡቲ ወደብ ላይ እንዲቀጥል ተደረገ። ስምምነቱን ተከትሎ፣"የኢ.ቴ.ኮ ማናጅመንት፣የሀገሪቷን የኢንተርኔት አቅም፣ከሦስት እጥፍ በላይ አሳደገ!" የሚለው ዜና፣በመንግሥት የሚዲያ አውታሮች ተሰራጨ። የመንግሥት ልሣን የኾነው አዲስ ዘመን ጋዜጣም፣የኢ.ቴ.ኮ ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩትን ግለሰብ በመጥቀስ፣ ስምምነቱ፣ከኹለት ዓመት በላይ ድርድር ተደርጎበት የተፈረመ መኾኑን በመግለጽ፣ አንባብያንን አስደመሙ። የሚገርመው ነገር ቢኖር፣ሲኮም (SEACOM)፣ 2.3 ቴራ ባይት ሰብማሪን ኬብል፣ሕንድ ውቅያኖስ ላይ ዘርግቶ፣በዓለም የመጨረሻው የብሮድባንድ ኢንተርኔት መዳረሻ ለኾኑት፣ለምሥራቅና ደቡም አፍሪካ ሀገራት፣የፈጣን ኢንተርኔት አገልግሎት ለማቅረብ የፈጀበት ጊዜ፣ሦስት ዓመት ብቻ መኾኑ ነበር። የሲኮም ኢንቬስተሮች፣ከ75% በላይ የሚኾኑት፣ አፍሪካውያን የነበሩ ሲኾን፣አጠቃላይ ኢንቬስትመንቱም፣750 ሚሊዮን ዶላር አይበልጥብም ነበር።

ነገር ግን፣ከላይ የተጠቀሰው ኢ.ቴ.ኮ፣ከሲኮም፣2.5 ጊጋ ባይት ኢንተርኔት ባንድዊድዝ ለመግዛት የከፈለው 47 ሚሊዮን ዶላር፣ሲኮም(SEACOM) ሲቋቋም አክሲዮን ቢገዛበት ኖሮ፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ከ100 ጊጋ ባይት ወይም 0.1 ቴራ ባይት ሊደርስ የሚችል፣ ኢንተርናሽናል ኮኔክሽን ልታገኝበት ትችል ነበር። ልብ ልንለው የሚገባው፣አኹንም፣ከ15 ዓመት በኋላም ቢኾን እንኳን፣የኢንተርናሽናል ኮኔክሽን አቅማችን፣100 ጊጋ ባይት አለመድረሱን ነው። ሀገር፣የካድሬዎች መጫወቻ ስትደረግ የሚደርሰው አደጋ፣ይኼንን ይመስላል። ኬንያ፣እ.ኤ.አ ማርች 2020 ላይ፣ ሞምባሳ ላይ ካገናኘችው፣ባለ12 ቴባ ሰብማሪን ኬብል በተጨማሪ፣ESSAT, SECOM, ESSAY ከተሰኙ ሰብማሪን ኬብሎች ጋር፣ኮኔክሽን ያላት ሲኾን፣የኬንያ መንግሥት፣ESSAY ሰብማሪን ኬብል ላይ፣35% የአክሲዮን ድርሻ አለው።

## ከቻይናው የመሠረተልማት ካምፓኒ ዚቲኢ (ZTE) ጋር የተደረገው ስምምነት

ኢ.ቴ.ኮ፣በካድሬዎች ደካማ አመራር ሥር በወደቀበት በዚያን ወቅት፣የአፍሪካን ገበያ ለመቆጣጠር አቅዳ ትንቀሳቀስ የነበረችው ቻይና፣ለወያኔ መንግሥት፣የብድር ስምምነት እንዲዋዋልና ዚቲኢ(ZTE) በተሰኘው መንግሥታዊ የቴሌኮም የመሠረተልማት ካምፓኒዋ አማካኝነት፣በመላው ሀገሪቱ የቴሌኮም መሠረተልማትን ለመዘርጋት የሚያስችል፣የ1.5 ቢሊዮን ዶላር፣የቬንደር ፋይናንሲንግ ስምምነት እንዲደረግ፣እድል የሰጠችው። በዚኽ፣

በተደረሰው ስምምነት መሠረት፣የቴሌኮም መሠረተልማቱ፣የ2ጂን እና 3ጂን ቴክኖሎጂ ሊያስተናግድ በሚችል ኹኔታ፣የፕሮጀክት ሥራው፣በተለያዩ ደረጃዎች የቴሌኮም ማስፋፊያ ፕሮጀክት 1-2 (TEP 1-2) ተከፋፍሎ ነው ዝርጋታው የተከናወነው። የኔትወርክ መሠረተልማቱ ዝርጋታ እንዳለቀ፣በወያኔ ካድሬና ወታደሮች የተሞላው የሥራ አመራር፣ይኽ የተዘረጋውን ከፍተኛ የኔትወርክ አቅም ሊጠቀም የሚችል ደንበኛ ለማፍራት የሚያስችል፣ የማርኬቲንግ ስትራተጂ ሊነድፉ የሚችሉ ስላልነበሩ፣ወያኔ፣ለኹለት ዓመት የሚቆይ የማናጅመንት ኮንትራት፣ከ30 ሚሊዮን ዩሮ በላይ በማውጣት፣ለፍራንስ ቴሌኮም (France Telecom) ለመስጠት ተገደደ።

## ከፍራንስ ቴሌኮም ጋር የተደረገው የማናጅመንት ስምምነት

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን (ኢ.ቴ.ኮ) የሚለውን ስም፣ወደ ኢትዮ ቴሌኮም በመቀየር ሥራውን የጀመረው፣የፍራንስ ቴሌኮም ማናጅመንት፣በመላው ሀገሪቷ የተዘረጋውን፣ የመሠረተልማት አቅም ለመጠቀም የሚያስችል ስትራተጂ በመንደፍ፣የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚውን፣በተለይም የሞባይል ስልክ ተጠቃሚውን ቁጥር፣ከ4ት ወደ 7፣ከ7 ወደ 14፣ከ14 ወደ 23 ሚሊዮን፣በኹለት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ፣እንዲያድግ አድርገውታል። በዚኽ በኹለት ዓመት ተኩል፣የፍራንስ ቴሌኮም ማናጅመንት ዘመን፣ብዙ የአገልግሎት ዓይነቶች፣በስፋት የተዋወቁና የዋጋ ቅነሳና ማሻሻያዎች እንዲተገበሩ እንዲኹም በርካሽ ዋጋ የሚገዙ የስልክ ቀፎዎች ለደንበኞች እንዲቀርቡ በመደረጉ፣በሀገሪቱ የነበረው የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ቁጥር፣በከፍተኛ ኹኔታ ሊጨምር ችሏል። እዚኽ ላይ፣የፈረንሣይ ማናጅመንት፣አንጻራዊ የሥራ ነፃነት የነበረው እንደመኾኑ፣የአገልግሎት ዘርፉን በተለይም የተገልጋዮችን ቁጥር በመጨመር ረገድ እንዲኹም የተገልጋዮችን እንክብካቤ (Custom-er Care) በማሳደግ፣ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ቢያስችለውም፣በእውቀት ሽግግር በኩል፣ሊሠራው ከሚገባው በታች ነበር - የሠራው። ይኽም የኾነበት ዋናው ምክንያት፣ሥራውን በቅልጥፍና ሊሠሩና የማናጅመንት ክህሎታቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉ፣በርከት ያሉ ንቁ ባለሞያዎች፣ከፍራንስ ቴሌኮም ማናጅመንት ባለሞያዎች ጋር፣ጎን ለጎን ኾነው እንዲሠሩ፣ዕድል ስላልተሰጣቸው ነበር።

## የኢንተርኔት በገጠር ከተሞች መስፋፋትና ሕዝባዊ አመጽ

ወያኔ፣የፍራንስ ቴሌኮም ማናጅመንትን ካሰናበተ በኋላ፣ተመልሶ፣የከፍተኛ የሥራ አመራሩን፣ ወደነበረበት፣ካድሬዎችና ወታደሮች ወደተሰገሰጉበት አስተዳደር እንዲመለስ ቢያደርግም፣ወያኔ እንዳሰበው፣ኹኔታዎች ሊኾኑለት አልቻሉም። የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚውን ቁጥር ማደግ ተከትሎ፣በተለይም በገጠሪቷ ኢትዮጵያ፣የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚው ቁጥር እየበዛ በመምጣቱ፣ከ2008ዓ.ም ጀምሮ፣በመላው ሀገሪቱ የተቀሰቀሰውን ፖለቲካዊ ይዘት ያለው አመጽ ለማቀጣጠል፣ዋነኛ መሣሪያ ኾኖ አገለገለ። ወያኔ፣ሕዝባዊ አመጹ ሲበረታበት፣ኢንተርኔቱን፣ ከ6ት ወር በላይ እስከመዝጋት ቢደርስም፣የዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ግፊት እያየለ በመምጣቱና የኢንተርኔት ፌስቡክ አብዮቱን መቋቋም ባለመቻሉ፣በ2010 ዓ.ም ለተደረገው የሥልጣን ሽግሽግ፣በር ከፍቷል።

## የኦዴፓ መራሹ ብልጽግናና የኢትዮ ቴሌኮም ሽያጭ ኹኔታ

በወያኔ ኢሕአዴግ እግር ሥር የተተካው ኦዴፓ ኢሕአዴግ፣የአኹኑ ብልጽግና፣ገና ወንበሩን ከመያዙ ሳምንት ሳይሞላው፣የቴሌኮም ዘርፉን፣ለውጪ ኢንቨስተሮች ሽያጭ እንደሚያቀርብ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት ማስታወቁ፣ብዙዎቻችንን፣ግራ ያጋባና ያስደነገጠ ጉዳይ ነበር። ይኽ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማስታወቂያ፣ከውጪ ኃይሎች በተደረገ ግፊትና ምንአልባትም ከወያኔ እጅ ላይ፣የሥልጣን ሽግግሩን ለማሳካት እንዲረዱ፣ለውጪ ኃይሎች እጅ መንሻ ቃል የተገባበት ጉዳይ እንደኾነ ይገመታል። ይኽን ግምት የሚያጠናክርልን ነገር ቢኖር፣ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣እ.ኤ.አ በ2018ቱ የዳቮስ የኢኮኖሚክ ፎረም ላይ ተጋብዘው፣ንግግር ባደረጉበት ወቅት፣የቴሌኮሙን ሴክተር፣ለውጪ ኢንቨስተሮች ገበያ ማቅረባቸውን ሲገልጹ፣ከሌሎች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጠቀሷቸው በርካታ ጉዳዮች በተለየ፣ከዓለም አቀፉ ግሎባሊስት ኢኮኖሚክ ኤሊት ታዳሚ የተቸራቸውን ጭብጨባ ስንመለከት፣ የቴሌኮም ሽያጩ ጉዳይ የውጪ ኃይሎች ግፊትና ተፅእኖ ሥር እየተከናወነ ያለ መኾኑን እንረዳለን። ዐዲሱ ተረኛ ኦዴፓ-ኢሕአዴግ የቴሌኮም ሴክተሩን ሽያጭ በአሁኑ ጊዜ ዋነኛ ጉዳዩ አድርጎ የሽያጭ ኺደቱን አማካሪ አድርጎ ከቀጠራቸው ከዓለም ባንክ እንዲኹም ከኢንተርናሽናል ፋይናንሻል ኮርፖሬሽንና ሌሎች የግሎባሊስቱ ማኅበረሰብ ጉዳይ አስፈጻሚ ድርጅቶችና አካላት ጋር በመኾን የሽያጩን ኺደት እያጣደፈው ይገኛል። ይኽ፣ያልበሰለ ጊዜያዊ ኢኮኖሚያዊ እንዲኹም ፖለቲካዊ ጥቅምን ብቻ ያማተረ ችኩል የመንግሥት እርምጃ፣ የሀገሪቷን ዘለቄታዊ የኢኮኖሚክ ሉዓላዊነት አሳልፎ የመስጠት፣የመጀመሪያው ምዕራፍ ተደግጎ ሊቆጠር ይችላል። ይኽን ሀቅ ለመረዳት፣ ከሽያጩ ሊገኝ የሚችለውን ጊዜያዊ ጥቅምና ዘለቄታዊ ጉዳት ስናጤን፣የምናገኘው እውነታ እንደሚከተለው ነው።

## ጊዜያዊ ጥቅም

መንግሥት፣ኢትዮ ቴሌኮምን፣በከፊልም ኾነ በሙሉ በመሸጥ፣በነስትራተጅር የተገመተለትን፣ ከ 15 እስከ 20 ቢሊዮን ዶላር ግምት ግማሽ ዋጋ

ቢያወጣለት፣ከ28 ቢሊዮን ዶላር በላይ እዳ የተጫነውን የሀገሪቷን የ110 ቢሊዮን ዶላር ኢኮኖሚ(GDP)፣ለጊዜው ከ5% እስከ 10% ሊያሳድግ ይችላል። ይኽን ጊዜያዊ እድገትና የውጪ ምንዛሬ ፍሰት ተጠቅሞ፣መንግሥት፣ጊዜያዊ ፖለቲካዊ ገጽታውን እንዲገነባ፣ሊረዳው ይችላል። በሌላ በኩል፣የቴሌኮም ሴክተሩን በሚቆጣጠሩት የውጪ ኢንቨስተሮች፣ዐዳዲስ አገልግሎቶች በፍጥነት ሲተዋወቁ፣ተገልጋዩን ኅብረተሰብ፣ለጊዜውም ቢኾን፣ሊያስደስተው ይችላል። ይኽ፣መንግሥት፣በችኩልነትና በውጪ ተጽእኖ ሥር እያካኼደው ያለው፣የኢትዮ ቴሌኮም ኩባንያ ሽያጭ፣ሊያስገኝ የሚችለው ውጤት ቢኖር፣ልክ ወያኔ የቢራ ፋብሪካዎቹን በቢሊዮን ዶላር በመሸጥ፣አግኝቶት የነበረውን ዓይነት ጊዜያዊ ትርፍ ማግኘት ብቻ ነው። ውሎ አድሮ፣“የማልጠግብ መስሎኝ በሬዬን አረድኩት!!” የሚለውን የአበው ብሂል፣እንድናስታውስ መኾናችን አይቀርም።

## ዘለቄታዊ ጉዳቱ

◈ መንግሥት፣የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅሙ ይዳከማል። ለምሳሌ ብንወስድ፣በአኹኑ ሰዓት፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣16ሺ ቋሚ ሠራተኞች ያሉትና ከ20ሺ ላላነሱ የኮንትራት ሠራተኞችና፣248 ዋና አከፋፋዮች 1348 ተቀባይ አከፋፋዮች እንዲሁም ከ247ሺ በላይ ቸርቻሪዎች የሥራ ዕድልን የፈጠረ ነው። ለውጪ ባለሃብቶች ፕራይቬታይዝድ ሲደረግ፣እንዲኽ ያለ፣ ሰፊ ቅጥርና የሥራ እድል፣ የመፈጠሩ ጉዳይ የማይታሰብ ነው። የውጪ ኢንቨስተሮች፣ዋናው የኢንቨስትመንት ዓላማቸው፣ትርፍ ነው። በመኾኑም፣በጥቂት ሠራተኛ፣ ብዙ ሥራን በማሠራት፣ትርፋማነታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው - ዓላማቸው። በ2011ዓ.ም፣ከፍራንስ ቴሌኮም ጋር የተደረገው የማናጅመንት ውልን ተከትሎ፣ከ3ሺ በላይ ሠራተኞች የተቀነሱበትን ማስታወስ፣በቂ ነው። የኢትዮ ቴሌኮም በሙሉ ወይም በከፊል መሸጥ፣በሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን፣የሥራ ዕድል እንደሚያሳጣ ይታወቃል። ምክንያቱም፣ኢትዮ ቴሌኮም፣ግማሽ የቢዝነስ አቅሙን ሸጦ፣ አኹን የያዘውን 16ሺ ሠራተኛ መሸከም የሚያስችል፣አቅም አይኖረውም። ላድርግም ቢል፣ ተወዳዳሪ መሆን ያቅተዋል። በመኾኑም፣የሚጠብቀው ዕድል፣ለቀጣይ ሽያጭ እራሱን ማመቻቸት ብቻ ይኾናል።

◈ የመንግሥትን የኢኮኖሚክ አቅም ምንጭ በማድረቅ፣የመንግሥትን አቅምን ያዳክማል። በመንግሥት አቅም ሊሠሩ የሚችሉ ትልልቅ ፕሮጀክቶች፣እንደ ሕዳሴ ግድብን የመሳሰሉ ፕሮጀክቶችን (state sponsored) የማካኼድ ዕድላቸው ይመናመናል። በመኾኑም፣ ፖለቲካው ከውጪ በመጣው ከበርቴ ግሩፕ የመጠለፍና ከሕግና ደንብ ይልቅ፣ለቢዝነስ ኢንተረስት ግሩፕ የመቆም ወይም የመገዛት ዕድሉ፣እየሰፋ ይኼዳል። የ"political market place" የሚባለው ዓይነት መንግሥታዊ አስተዳደር እንዲሰፍን፣በር ይከፍታል።

◈ መንግሥትና ኅብረተሰቡ፣በማኅበራዊና ብሔራዊ ጥሪ አማካኝነት የሚያገኙትን፣የገንዘብና ያገልግሎት ድጋፍ ያጣሉ ። ለምሳሌ፣ባለፈው ዓመት 2012 ዓ.ም ብቻ፣ኢትዮ ቴሌኮም፣ ለኮሮና ወረርሽኝ ያደረገውን የ772 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ጨምሮ፣ከ1.15 ቢሊዮን ብር የሚደርስ፣ለመንግሥትና ለኅብረተሰቡ ድጋፍ ሰጥቷል። የዐዲስ አበባው ቀላል ባቡር ፕሮጀክትም የተገነባው፣ከቴሌኮም ሴክተሩ በተገኘ ትርፍ ጭምር መኾኑንም፣ማስታወስ ይቻላል።

◈ የቴሌኮም ሴክተሩን የሚቀራመቱት የውጪ ኩባንያዎች የገንዘብ አቅም፣ ከፍተኛ ስለሚኾን፣የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችና ባለሞያዎች ተደራጅተው፣በቴሌኮም ዘርፍ ሊሳተፉ የሚችሉበትን ዕድል ይዘጋል። በአፍሪካ ሀገራት ያለውን ልምድ እንደምናየው፣ተወዳዳሪ ሊመጣ የሚችለው፣በቀጥታ ከውጪ ኩባንያዎች ብቻ ይኾናል። ለምሳሌ፣የአፍሪካን ከ40 በላይ የኾኑ የቴሌኮም ኦፐሬተሮች ቢዝነስ ብንቃኝ፣በከፊል በመንግሥት የአክሲዮን ድርሻ ከታየዙት ኦፐሬተሮች በስተቀር፣በአፍሪካውያን ባለሃብቶች፣ሙሉ በሙሉ የተያዙት ኦፐሬተሮች፣ከአንድና ሁለት የዘለሉ አይደሉም። በዚኽ ረገድ፣በናይጀሪያዊው ማይክ አዴኑጋ (Mike Adenuga) ባለቤትነት የተያዘው፣45 ሚሊዮን ደንበኞች ያሉት "ግሎ ሞባይል (glo mobile)" ፣ለናይጀሪያውያን ኩራት ነው።

◈ ኢትዮጵያ፣ ይብዛም ይነስ፣እስካኹን፣በራስዋ ልጆች እውቀት የምትተማመን ሀገር የነበረች መኾኗ፣የሚታወቅ ነው። አኹን፣እራሱን ለማሸጋገር እየተንደረደረ ያለው፣አዴ.ፓ መራሹ የብልጽግና መንግሥት፣በኢትዮጵያውያን ባለሞያዎችና የቢዝነስ ሰዎች እንዲኹም ባለሃብቶች፣እምነት በማጣት፣ሊወስድ የተዘጋጀውና እየወሰደ ባለው ትልልቅ የመንግሥት ኩባንያዎችን ለውጪ ባለሃብቶች የመሸጥ ችኩል እርምጃ፣የሀገሪቷን የኢኮኖሚክ ሉአላዊነት፣ቀስ በቀስ አሳልፎ የመስጠት ጉዞውን፣ሀ ብሎ ጀምረው ማለት ነው። እንደ ኬንያዊው ፕሮፌሰር ፓትሪክ ሉሙምባ እንዲኹም ጀሸዋ ኦፔንጋ፣በአፍሪካ ደረጃ የታወቁ፣የአፍሪካ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ልሂቃን አስተያየት፣አፍሪካ በአኹኑ ሰዓት፣ በአውሮጳውያንና በቻይናውያን የኢኮኖሚክ ቅኝ ግዛት ውስጥ ያለች አህጉር ናት ። በአፍሪካ፣በየሃገሪቱ የሚገኙ መሠረታዊ የባንኪንግ፣የኢንሹራንስ፣የማእድን፣የቴሌኮምን የመሳሰሉት ኢንዱስትሪዎች፣በአውሮጳውያን ባለሀብቶች የተያዙ ናቸው። የአፍሪካ ኢኮኖሚ፣በአጭሩ፣በአውሮፓውያንና በቻይናውያን እጅ ውስጥ የወደቀ ነው። ፈረንሣይ ብቻዋን፣ ወደ 15 ሚጠጉ ቤኒን ፣ ቡርኪናፋሶ ፣ ጊኒቢሳኦ ፣ አይቮሪኮስት ፣ ማሊ ፣ ኒጀር ፣ ሴኔጋል ፣ ቶጎ ፣ መካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ካሜሩን፣ጋቦን፣ኢኳቶሪያል ጊኒ እንዲኹም ኮንጎ የምዕራብና መካከለኛው አፍሪካ የቀድሞ ፈረንሣይ ቅኝ ሃገራትን ኢኮኖሚ ተቆጣጥራለች ። እነዚኽ ሀገራት የሚጠቀሙት ገንዘብ፣የፈረንሣይ ፍራንክ ሲኾን፣የብሔራዊ ሪዘርቭ ገንዘባቸውን 85% የሚያስቀምጡት፣ፓሪስ በሚገኘው በፈረንሣይ ሴንትራል ባንክ ሥር ብቻ ነው። ገንዘብ መበደር ሲፈልጉ እንኳን፣የራሳቸውን ገንዘብ፣በወለድ ነው - የሚበደሩት። እንደ ዶ/ር ኤሪካና ቺሃምቦሬ፣የቀድሞ በአሜሪካን ኒውዮርክ የአፍሪካ አንድነት አምባሳደር መረጃ ከኾነ፣ከምዕራብ አፍሪካ ብቻ፣ወደ 500 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ሀብት፣በየዓመቱ፣ወደ ፈረንሣይ ባንኮች፣ፈሰስ ይደረጋል። በምዕራብ አፍሪካ ሀገራት፣በአኹኑ ጊዜ፣ከፈረንሣይ የኢኮኖሚክ ቅኝ ግዛት ለመላቀቅ፣በምዕራብ አፍሪካ የጋራ ኢኮኖሚክ ማኅበር (ECOWAS) በኩል፣ከፍተኛ ትግል እያደረጉ ይገኛሉ። ኢኮ (eco) የተሰኘ የጋራ ገንዘብና ነጻ የጋራ ገበያ ለማቋቋም የሚያስችላቸውን ስምምነትም ተፈራርመው፣ወደተግባር እየገቡ ነው። የእነዚኽን የአፍሪካ ሀገራት ልምድ ስናይ፣ምንም እንኳን በአኹኑ ሰዓት፣ኢትዮጵያ ያለችበት የፖለቲካና የኢኮኖሚክ ኹኔታ፣ከብድርና ከእርዳታ አዙሪት አላስወጣ ብሎ ቢይዛትም። ለኢትዮጵያ ሀገራችን ዘለቄታዊ እድገት የምናስብ ከኾነ፣የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን አቅም ማሳደግ፣ አማራጭ የሌለው አቅጣጫ መኾኑን እንረዳለን። ይኽን ለማድረግ ደግሞ፣መንግሥት፣ ትልቁን ሚና መጫወት የሚያስችለውን፣በእጁ የያዛቸውን ትልልቅ ኩባንያዎች፣ለውጪ ባለሀብቶች ከማዘዋወሩ በፊት፣ወደ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እጅ ሊገቡ የሚችሉበትን መንገድ፣መቀየስ ይጠበቅበታል። በኢትዮጵያ ያሉ የግል ባንኮች የተቋቋሙት፣ቀደም ሲል፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውስጥ ይሠሩ በነበሩ፣ልምድ ባላቸው ባለሞያዎች አማካኝነት ነበር። ይኽ ዕድል፣መንግሥት፣ለባንክ ባለሞያዎች ከዚኽ ቀደም እንደሰጠው ኹሉ፣በኢትዮ ቴሌኮምም ኾነ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ይሠሩ የነበሩ ነባር ባለሞያዎች፣የየሴክተራቸውን የግል ኩባንያ እንዲያቋቁሙ፣ዕድሉን መንግሥት ሊያመቻች ይገባል። ይኽን በማድረግ፣ ወደፊት ሊመጡ ከሚችሉ የውጪ ኩባንያዎች ጋር፣ተፎካካሪ የሚያደርጋቸውን የማናጅመንት እና የካፒታል አቅም ሊገነባላቸው ይችላል። የኤየርላይንስም ኾነ የቴሌኮም ቢዝነስ፣ዋናው አቅም የሚጠይቀው ማናጅመንት ነው። ለረጅም ጊዜ ፖለቲካውን ከሚመሩት

አምባገነኖች የሚመነጩ፣እንጭጭ አስተሳሰቦችና ተጽዕኖዎች፣ነፃ የነበሩና ያልተበረዙ የማናጅመንት አመራር የነበሯቸው፣እንደ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ ትልልቅ ኩባንያዎች፣ለረጅም ዐሥርት ዓመታት፣በዓለም ደረጃ ያሳዩት ተወዳዳሪ የኾነ የማናጅመንት ብቃት፣በሌሎች እንደ ኢትዮ ቴሌኮምና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባሉ ግዙፍ ኩባንያዎች ለመድገም፣የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ችግር ካልኾነ በስተቀር፣የእውቀት ችግር እንደማያግዳቸው፣ለመረዳት እንችላለን። የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣የአፍሪካ ሀገራት ሕዝቦች ኩራት እና አርአያ አድርገው የሚመለከቱት ኩባንያ መኾኑንም፣ማስታወስ አለብን። የኢትዮጵያን አየር መንገድ፣አሳልፎ ለአውሮፓውያን ወይም ለቻይና ወይም ለዐረብ ሀገራት ባለሐብቶች መሸጥ፣የአፍሪካውያንንም ቅስም የሚሰብር እንደኾነ፣ልናውቅ ይገባል። በመኾኑም፣መንግሥት፣ልክ እንደ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣በየሴክተሩ፣ትልልቅ አገር በቀል ኾነው፣አገር ዘለል፣በተለይ በአፍሪካን ሰፊ ገበያ ላይ ሊያተኩሩ የሚችሉ ኩባንያዎችን እንዲያቋቁሙ፣መሥራት ይጠበቅበታል። ነገር ግን፣አኹን፣"ሀገሪቷን እያሻገርኩ ነው!!" የሚለው መንግሥት፣ጊዜያዊ የፖለቲካልና ኢኮኖሚክ ጥቅምና ትርፍን በማስላት፣ኢትዮ ቴሌኮምን በመሸጥ የጀመረውን ጉዞ፣ ወደ ባንኮቹና ኢንሹራንሶቹ፣ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ማሪታይም ትራንዚት፣ወደ ምድር ባቡር እና የስኳር ኮርፖሬሽን ከቀጠለ፣እንደ አያያዙም ከኾነ፣የሚቀጥል ይመስላል። ኢትዮጵያ፣እንደ አፍሪካውያን መንግሥታት፣ያላትን ኹሉ ሸጣ፣ባዶ እጇን የምታጨበጭብበት ጊዜ፣እሩቅ አይኾንም። ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የመጣውን፣ኢትዮጵያውያን እንኮራበት የነበረውን፣በራስ የመተማመንና በራስ አቅም የማደግ መንፈሳችንን፣ሰባብሮ የሚጥልም ይሆናል። አኹን፣የአፍሪካ ሀገራት ለመመለስ ሚታገሉለትን የኢኮኖሚክ ነፃነት፣በገዛ እጃችን፣አሳልፈን ለውጪ ባለሀብቶች በማስረከብ፣የመጪውን ትውልድ ዕጣ ፈንታ፣በኢኮኖሚክ ባርነት ውስጥ፣የሚከተው ይኾናል።

## በምርጫ የሚያሸንፍ መንግሥት፣ሊያያቸው የሚገባቸው አማራጮች

1. የአምስት ዓመት እቅድ ወስዶ፣የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ከነባርም ኾነ ዐዳዲስ ባለሞያዎች ጋር ኾነው፣የኢትዮ ቴሌኮምን የተለያዩ ሴክተር ሥራዎችን፣በአውትሶርሲንግ በመስጠት፣ የቴሌኮም ሴክተሩን ሥራ፣ልምድ እንዲያገኙበት እንዲኹም የገንዘብ አቅማቸውንም እንዲያደረጁ ማገዝ። ለምሳሌ፣የቴሌኮም መሠረተልማቱን የጥገና ሥራ፣የፋይበር ኬብል ዝርጋታ ሥራን ለሀገር ውጥ ባለሞያዎችና ባለሀብቶች ጥምረት ለሚፈጠሩ ኩባንያዎች፣አውትሶርስ ማድረግ። እዚኽ ላይ፣ የቻይናን ምሳሌ ብንመለከት፣አኹን፣የዓለምን የቴሌኮምና የኦንላይን ንግድ እየተቆጣጠሩ የመጡት፣እንደ ሁዋዌና አሊባባ ያሉት፣ጠንካራ የዓለማችን የቴክኖሎጂ ካምፓኒዎች፣አኹን የደረሱበት ለመድረስ፣የቻይና መንግሥት ያደረገላቸው አስተዋፅኦ፣ እጅግ ወሳኝ ነበር። በቻይና መንግሥት ድጋፍ እየተደረገላቸው የተቋቋሙ፣የግል የቢዝነስ ተቋማት ያፈሯቸው የቻይና ኢንተርፕሬነር ቢሊየነሮች፣እ.ኤ.አ በ2020፣የሀብት መጠናቸው፣ ከ4.3 ትሪሊየን የዘለለ ኾኗል። ይኽም፣የአፍሪካን 3.3 ትሪሊየን አጠቃላይ ኢኮኖሚ፣በትሪሊየን ዶላር የሚበልጥ ነው። የቻይና ፈጣን እድገት የተመዘገበው፣መንግሥትና ኢንተርፕሬነሮችዋ በጋራ፣ለአንድ ዓላማ፣'ቻይና'ን በጥምረጥ፣በመሥራታቸው ነው። ለእኛም ሀገር ኢንተርፕሬነሮችና ባለሀብቶች፣የኢትዮጵያን ዕድገት ዓላማው ያደረገ የመንግሥት ድጋፍ፣ሊሰጣቸው ይገባል:: መንግሥትና የኢትዮጵያ ኢንተርፕሬነሮችና ባለሀብቶች፣የጋራ ዓላማቸው ለኾነችው 'ኢትዮጵያ'፣በፍጹም ታማኝነትና ሀገር ወዳድነት፣በጥምረት ሊሠሩ የሚችሉበትን፣ለዘመናት የሚዘልቅ ስትራተጂካዊ አሠራር መቀመር ይጠበቅበታል።

2. የቴሌኮም መሠረተልማት ግንባታ ፈቃድን፣ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ከመንግሥት ጋር ኾነው እንዲገነቡ ማድረግ። ለምሳሌ፣ኢትዮጵያ፣የራሷ ኢንተርናሽናል ሰብማሪን ኬብል የምትዘረጋበትን ዕድል፣ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እንዲገቡበት ማገዝ፣ማበረታታትና መርዳት።

3. ዲያስፖራውን፣አዋጪነቱ በማያጠራጥረው በቴሌኮም ዘርፍ እንዲሳተፍ በመጋበዝ፣ መንግሥት፣የቴሌኮም ሴክተሩን፣ወደ ግል ይዞታ በማዘዋወር ያገኛል ተብሎ የሚታሰበውን የውጪ ምንዛሪ፣በቀላሉ እንዲያገኝ ማድረግ። በውጪ፣በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ በሀገራቸው ኢኮኖሚክ ዕድገት፣ቀጥታ ተሳታፊ እንዲኾኑ ማድረጉ፣ኢትዮጵያን፣ከዲያስፖራው ሊገኝ የሚችሉ በርካታ ተዛማጅ ጥቅሞችን ማግኘት እንድትጀምር፣ማድረግ ያስችላታል። በሌላ በኩል፣የዲያስፖራው ማኅበረሰብ አባላት የዜግነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣ዕድል ይከፈታል፤ ብሎም፣በዜግነታቸው ማግኘት የሚገባቸውን፣የሞራልም ኾነ የኢኮኖሚክ ጥቅም እንዲያገኙ፣ ማድረግ ያስችላል።

4. በአብዛኛው፣ ከ70% በላይ፣በወጣትነት ዕድሜ ላይ ባሉ ሠራተኞች የተሞላውን፣የኢትዮ ቴሌኮም ሠራተኛ፣ከ5 እስከ 10 ከመቶ የሚደርስ፣የኩባንያቸውን የኢትዮ ቴሌኮም የአክሲዮን ድርሻ እንዲገዙ ወይም በስጦታ እንዲያገኙ በማድረግ፣መጪው ትውልድ፣ተስፋው የለመለመ፣ ሀገር ወዳድ፣በቴሌኮም ዘርፍ፣ከሀገር ውስጥ አልፎ ድንበር ተሻግሮ፣ትጉኽ ተወዳዳሪ ሠራተኛ እንዲኾን ማድረግ ይቻላል።

5. ኢትዮጵያ በአኹኑ ሰዓት፣አንድ ሦስተኛው ኢኮኖሚዋ(GDP)፣ብድር መኾኑ የታወቀ ኾኗል። እንደዚያም ኾኖ፣ሀገራችን ጠንካራ የፖለቲካ አመራር ካገኘች፣ከዚህ ብድር አባዜ፣እጅግ በጣም አጭር በኾነ ጊዜ ውስጥ የምትወጣበት ዕድል፣ለመፍጠር ትችላለች። ይኽንንም ለማድረግ የምትችለው፣የራስዋን የሰው ኃይልና የኢኮኖሚክ አቅም በማሳደግ ላይ፣አተኩራ በመሥራት ብቻ ነው። በውጪ ኢንቨስትመንት ላይ፣ጥገኛ የኾነን የኢኮኖሚክ ዕድገት የምንመኝ ከኾነ፣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ፣መላው ኢኮኖሚያችንን፣ፖለቲካውንም ጨምሮ፣ለውጪ ኃይሎች አስረክበን፣ቁጭ እንላለን። አባቶቻችን፣በደማቸው ያቆዩልንን፣የእምቢ ባይነት በራስ የመተማመን ብሔራዊ ሀብት እናጣለን።

6. በመንግሥት እጅ የሚገኙትን ኢትዮ ቴሌኮምንና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ጨምሮ፣ ሌሎችንም ትልልቅ ድርጅቶች የማናጅመንት ሥራ፣ከፖለቲካ ሹመትና አጉዋጉል ጣልቃ ገብነት ተፅእኖ ነፃ በማውጣት፣ለቦታው ተመጣጣኝ አቅምና ልምድ ባላቸው ባለሞያዎች እንዲመሩ ማድረግ። ይኽን በማድረግ፣የተቋማቱን ዕድገትና ትርፋማነት በማረጋገጥ፣ የሀገሪቷን ኢኮኖሚና ቢሮክራሲ፣ጠንካራ መሠረት ላይ እንዲወድቅ ማድረግ ይቻላል። ዐዲሱም ትውልድ፣በእነዚኽ ተቋማት ውስጥ፣በተገቢው መንገድ፣ሙያዊ ብቃቱን የሚያሳድግበትንና ልምድ የሚቀስምበትን ዕድል፣ማመቻቸት ይገባል። የግል ሴክተሩም፣አግባብና ሙያዊ ብቃት ባለው ማናጅመንት ከሚመሩ፣ትልልቅ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ በሚወጡ፣ከፍተኛ ልምድ በሚኖራቸው ባለሞያዎች፣አቅሙን ሊያጎለብትና የሥራ መስኩን፣ሊያስፋፋ ይችላል።

# አወይ እኔነቴ

ጅምሬ ቀዳሚ
ጉዞዬ አድካሚ
ውጣ ውረድ ያለው
ከሚዛኑ ዝንፍ ወይፍንክች የሌለው
ከአፈር በቅዬ
በአፈር አብቅዬ
አፈር እየገፋው አፈር የሚገፋኝ
አፈር እየበላው አፈር የሚበላኝ
ማብቀያም ዘርም ነኝ
በአንድነቴ ውስጥ ህብረ-ቀለም ያለኝ
ሀዘኔን፣ ደስታዬን የምቋጭ በስንኝ
የዘመን ውኹምብር የማይሸረሽረኝ
ባቋሜ ጸንቼ በቃሌ የምገኝ
ሲጠልፉኝ አቅንቼ ሲገፉኝ የምሸኝ
ቀለምን ጠንቅቄ በቃሌ እምወጣ
ከምንጩ ቀድቼ ከምንጩ እምጠጣ
በሀሳብ ወጥኜ በምግባር ተስዬ በግብር የምወጣ
የተላለፈኝን አይቀጡ ምቀጣ
የተማመነኝን ፍቅር የማጠጣ
አወይ እኔነቴ
ከጥንቱ ቀድቼ የነገን ማስላቴ
የማይመነዘር ዝንጉርጉርነቴ
ምናቤ እምቅ ንግግሬ ቅኔ
በቀኙ ውዬ የማድር በጎኔ
መነሻዬ ብእር መቋጫው ምናኔ
እራሴው ቋጥሬ እራሴው ምፈታ
በጊዜ ማልቃኝ በስፍር በቦታ
በማለዳ አፍርቼ የምበስል ማታ
የሆንኩትን ሁኜ ያልሆንኩትን ያልሆንኩ
በጥበብ መጥቄ ሰማይን የታከኩ
በስጋ ቀጥኜ በመንፈስ የወፈርኩ
በትውልድ ቅብብል እየተሰናሰልኩ
ጥንቴንም ዛሬዬን ነገዬንም ያከልኩ
ፊደልን ጠንቅቄ በእውቀት የበሰልኩ
በምድር እየኖርኩ በሰማይ የነገሥኩ
የጽድቅ መንገዴን መድረሻዬን ያወኩ
መንጠላጠያዬን መሰላል የጨበጥኩ
ወድቆ አለመቅረትን ያወኩኝ ጠንቅቄ
ከቅርቡ እያደርኩኝ የማስብ አርቄ
በሀሳብ አቅርቤ በምናብ አርቄ
የሩቁን ከቅርቡ በውል ደባልቄ
በውኹንብር ዓለም የምገኝ ጠንቅቄ
የማመልክ በስሉስ
ከአጸዱ ውዬ የማድር ከመቅደስ
የምምል በማሪያም
አርማዬ ሶስት ቀለም
አወይ እኔነቴ ኢትዮጵያዊነቴ፡፡

*(ቢቃሉ ሰውመሆን)*

# ታሪክ ምስክር ነው

ይላል የቀድሞ ሰው ጉድ ነው የፍንጅርቱ
እናቲቱን አንች ልጅዬውን አንቱ
ማድረጉ ሲገርመው ሴንጮን አማካሪ እስኬውን ታሳሪ
ብሎ እያጠየቀ የመሪ ተግባር ነው? ወይስ የመሰሪ?
እንግዲህ ኢትዮጵያ ጠንክረህም ታገል ከችግር ተማር
ባልደራስ መጣልህ እራሱነን ፈቶ ፍፁም ነፃወጥቶ ከህሊና እስር በፍፁም ተላቆ ከፍርሃት ቆፈን
መሪውን አድርጎ ታላቅ እስክንድር
ስንታዬው ይልሃል አሻግሮ ሲያማትር
ቀለቡን ሰንቆ ወንዝ የሚሻገር
በአስካል በፀዳሉ ተውቦ በሀገር
በትግል ጠንክሮ ምርጫን አሸንፎ  ሊያፀና ሀገር
ይመስገን ይወደስ  ከባደረቦቹ ታጋይ እስክንድር ታላቁ እስክንድር፡፡
በቦሌም በየካ ባልደራስ ለምልሟል
በአዲስ ከተማና በአራዳም አብቧል
በኮልፌ ነፋስ ስልክ በአቃቂም አሸቷል
በቂርቆስ ጉለሌ ልደታም አፍርቷል
መላው አዲስ አበቤ በሙሉ ኢትዮጵያ ከባልደራስ ጋራ ለድል ተዘጋጅቷል
ባልደራስ ሲያሸንፍ ባልደራስ ድል ሲያደርግ ሁሉም ሰላም ይሆናል፡፡
ሀገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላለ የሞተልሺ ሳይሆን የገደለሽ በላ
እንዳይሆን ተረቱ ከአሁን በኋላ አሳልፎ የማይሰጥ ድሉንም ለሌላ
ይፈጠራል ዜጋ ይፈጠራል ወጣት በእውቀት የተሞላ ወኔው የማይላላ
የጀግና ልጅ ጀግና የእሳት ልጅ እረመጥ ይሉሀል፣ ይሉሻል ይሄ ነው
የቴዎድሮስ ልጁ የሚኒሊክ ወንድም የበላይ ዘለቀ የንጉስ ሚካኤል የአብዲሳ አጋም ነው
ለሀገሩ ሞቶ ወገኑን ያኖረው
(በካድራ ወንዝ) ሞቶ ኢትዮጵያን ያኖረው
በፍጹም አይሞትም በጭራሽ አልሞተም ምን ጊዜም ህያው ነው
ጊዜ የሚያወጣው ጊዜ የሚገልጠው ታሪክ ምስክር ነው፡፡

ውቤ ደነቀው መኮንን 


ኢትዮጵያ ዳግም
የህሊና እስረኞች
ቤት እንድትሆን
መፍቀድ የለብንም!
ባልደራስ
ለእውነተኛ ዲሞክራሲ